Harla Journals

Harla Journal of Social and Behavioral Studies

Journal home page: https://journals.ddu.edu.et/index.php/HJSBS

Harla journal
of Social and Behavioral Studies

# የጨነገፈ ፍቅር፡ ስነ-ሂሳዊ ፍከራ በመንግስቱ ለማ የፍቅር ግጥሞች

# An Aborted Love: Literary Interpretation of Love poems (on the poetry collection of Mengistu Lemma)

**ነጋ አበራ***

*Nega Abera*
**Assistant Professor at Department of Amharic Language and Literature, College of Social Science and Humanities, Dire Dawa University, Dire Dawa, Ethiopia, Email: negabera2011@gmail.com Phone: +251974019844*

**አጠቃሎ (Abstract)**
*ይህ ጥናት የተካሄደው በሀገራችን "ለመጀመሪያ ጊዜ" የፍቅር ግጥሞች ታትመው በቀረቡበት የግጥም መድበል ውስጥ ነው፡፡ ግጥሞቹ የተፃፉት በአንጋፋው የስነጽሑፍ በመንግስቱ ለማ ሲሆን መድብሉም "የግጥም ጉባኤ" በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመው እ.ኢ.አ በ1950 ዓ.ም ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ ስነግጥማዊ ትንተና እና ፍከራ በማካሄድ በመድብሉ ውስጥ ወጥነት ያለው የፍቅር ታሪክ መተረኩን መመርመር ነው፡፡ ጥናቱም ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የተከተለው "ፈካሪ" (interpretative) ተብሎ የሚጠራውን የምርምር ስነዘዴያዊ ንድፍ ነው፡፡ ይህን ንድፍ የተከተለ ስነግጥማዊ ስነሂስ በማካሄድ በመድብሉ የተካተቱ ግጥሞችን መርምሯል፡፡ በዚህም መሰረት ጥናቱ በመድብሉ ውስጥ ከተካተቱት 26 ግጥሞች መካከል፣ ከፊል የሚሆኑት፣ 12ቱ የፍቅር ግጥሞች መሆናቸውን ደርሶበታል፡፡ ከ12ቱ መካከል በ9ኙ የፍቅር ግጥሞች ላይ ጥብቅ የእርስ በእርስ ትስስርና ዝምድና ተገኝቷል፡፡ ትስስር ከተገኘባቸው 9 ግጥሞች መካከል በ6ቱ ውስጥ ወጥነት ያለው የፍቅር ታሪክ መተረኩ ተደርሶበታል፡፡ በውዳሴ ጀምሮ፣ በጥበቃ ገስግሶ፣ በስንብት የሚቋቸው ይህ የፍቅር ታሪክ በ3 ምዕራፎች ሊከፈል እንደሚችል ጥናቱ አሳይቷል፡፡ በግጥሞቹ የቀረበው የፍቅር ታሪክም የቆየው ከልጅነት እስከ ጉልምስና እድሜ እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡ ይህ ረጅም ጊዜን የፈጀ የፍቅር ታሪክ በግጥሞቹ ውስጥ ይተረክ እንጂ ገና በፅንስነት ለጋ እድሜው የጨነገፈ፣ በጅምር የቀረ፣ ያልተሳካ ፍቅር መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡*

**ቁልፍ ቃላት (Keywords) ፡** "የፍቅር ግጥሞች" ፣ "ፈካሪ" ምርምር,

*This study was conducted on the poetry collection in our country where love poems were published and presented "for the first time". The poems were written by the renowned literary figure Mengistu Lemma, and the collection, titled "የግጥም ጉባኤ" ("The Assembly of Poems"), was first published in 1950 E.C. The main objective of this study is to conduct a poetic analysis and interpretation to examine whether a coherent love story is narrated within the collection. To achieve this objective, the study followed a research methodological design called "interpretative". By employing this design, it examined the poems included in the collection through poetic criticism. Accordingly, the study found that out of the 26 poems included in the collection, a portion, specifically 12, are love poems. Among these 12, a strong interconnectedness and relationship were found in 9 love poems. Among the 9 interconnected poems, a coherent love story was found to be narrated in 6 of them. The study has shown that this love story, which begins with praise, progresses through anticipation, and concludes with farewell, can be divided into 3 chapters. It is also estimated that the love story presented in the poems spans from childhood to adulthood. The study confirms that although this long-lasting love story is narrated in the poems, it is an unsuccessful love that was aborted at its nascent stage, left incomplete, and did not succeed.*

**Keywords:** Interpretive research, love poems

**Corresponding author: Nega Abera, negabera2011@gmail.com , Cellphone: +251974019844*
*DOI:*



*© 2024 Harla Journals and Author(s). Published by Dire Dawa University on Open Access Policy under CC-BY-NC 4.0.*
*Received March 2024; Received in revised form May 2024; Accepted June 2024*

# 1. መግቢያ (Introduction)

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ፍቅር ከስሜት ጋር የተቆራኘ ኑረት ያለው ሰብዓዊ እሳቤ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜም ከስነፅሁፍ ዘርፎች መሀል ስለፍቅር የሚፃፈው በግጥም ነው፡፡ “ግጥም የህያው ስሜቶች ምስክርነት እንደሆነ እናምናለን” ብሎ እንደፃፈው ገጣሚ በእውቀቱ ስዩም (1996)፣ ከስሜት ጋር ባላቸው ጥብቅ ቁርኝት ምክንያት ፍቅርና ግጥም ብዙውን ጊዜ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ ሆነው በኪነጥበቡ አለም ይገኛሉ፡፡

በስነግጥም ጥናት ውስጥ የፍቅር ግጥሞች የሚመደቡት ሊሪክ (lyric) ከሚሰኘው የግጥም ምድብ ውስጥ ነው፡፡ የፍቅር ግጥሞች ዓይነታቸው ብዙ ሲሆን አራት ዋና ዋና የወል ባህሪያት እንዳላቸው ብርሃኑ ገበየሁ “ቀጥተኛነት፣ የስሜት ጥልቀትና ፍላት፣ ዜማዊነት፣ ግላዊነት/እኔነት/” *(2001፥ 179-180)* ናቸው በማለት ይገልፃል፡፡

> *የፍቅር ግጥሞች ቀጥተኛ ናቸው ስንል፣ እንደ ዘፈን፣ እንደ ጸሎት ደራሹ ድምፅ /ተናጋሪው/ ተደራሹ/ዋን ገጸሰብ በግንባር ነው እሚያናግረው፣ “እኔ-አንተ/አንቺ” በማለት፡፡ በሌሎቹ የሌሪክ ንዑስ ዝርያዎች የተለመደ ቢሆንም፣ የፍቅር ግጥሞች እጅጉን ስሜት ንክር፣ በጣሙን ከጥልቅ ልቡና የሚፈሱ ናቸው፡፡ ስለዚህም አገላለጹ ስሜትን ይነዝራል፣ ወይም ልብን ያሞቃል. . .ከጥልቅ ነፍስ ውስጥ፣ በድንገት ፈንቅሎ የሚፈስ ኃይል ስሜት ሙዚቃዊና ዜማዊ ሲሆን የእንጉርጉሮ. . . የመባባት ወዘተ ስሜትን ያሰርጻል. . . . (2001፥ 179-180)*

ከ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ በፊት በነበረው ዘመን እንደነዚህ አይነት ባህሪያት ያላቸው የተቃራኒ ፆታ ፍቅር ግጥሞች በሀገራችን ባህልና እሴት ተፅዕኖ ምክንያት በአደባባይ አይፃፉም ወይም አይነገሩም ነበር፡፡ የፍቅር ግጥሞችም ከሀገራችን ዘመናዊ የአማርኛ ስነግጥም ጋር በግልፅ የተዋወቁት ከ1950ዎቹ በኋላ መሆኑን ብርሃኑ ገበየሁ እንዲህ በማለት ይገልፃል፡፡

> *የአማርኛ ገጣሚያን በተለይ የፍቅር ግጥሞችን (ሥጋዊ ፍቅር) መግጠምና ማሳተም የጀመሩት ከ1950ዎቹ ጀምሮ ነው ማለት ይቻላል፥፥ ይህንን እውነት ለማስረገጥ ሩቅ መሄድ አስፈላጊ አይደለም፡፡ የዘመናዊው የአማርኛ ሥነ ግጥም መስራች ከበደ ሚካኤል በግጥሞቻቸው ያላነሱት ሰብዓዊ ጉዳይ አለ ቢባል፤ ሲጋዊ ፍቅር ብቻ ነው፡፡ (2001፥ 178)*

የብርሃኑ ገበየሁ ጥናት እንደተመለከተው፣ 1950ዎቹ የፍቅር ግጥሞች ለህትመት የበቁበት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ስነግጥም “ላቅ ወዳለ ኪነጥበባዊ ደረጃ” የተሸጋገረበት ነው (2001፡ 183)፡፡ በዚህ ምሁር የዘመን አከፋፈል መሰረት በዚህ ዘመን ከተነሱ ፋና ወጊ ገጣሚያን መካከል በፍቅር ግጥሞቻቸው የሚታወቁት መንግስቱ ለማ፣ አፈወርቅ ዮሐንስ፣ ዮሐንስ አድማሱ፣ ፀጋዬ ገብረመድህን፣ ገብረ ክርስቶስ ደስታ፣ ሰለሞን ደሬሳ ዋነኞቹ ናቸው (2001፡ 179)፡፡

ከነዚህ ስመ ጥር ገጣሚያን መካከል የአማርኛ ዘመናዊ የፍቅር ግጥሞችን ያስተዋወቁት መንግስቱ ለማ ናቸው፡፡ መንግስቱ ለማን የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ ታሪክ የሚያነሳቸው በሁለገብነታቸው ማለትም በግጥም በተውኔትና በአካዳሚያዊ መጣጥፍ ጸሐፌነታቸው ነው (መስፍን ዓለማየሁ፣ 1988፡ 238)፡፡

እኚህ ገጣሚና ጸሐፌ ተውኔት ለመጀመሪያ ጊዜ የፍቅር ግጥሞችን ያሳተሙት “የግጥም ጉባኤ” በሚል ርዕስ፣ በ1950 ዓ.ም ባሳተሙት የግጥም መድብል ነው፡፡ ከዚህ ፈር ቀደጅ ስራ በኋላ የፍቅር ግጥሞች በከፍተኛ ደረጃ በሌሎችም ገጣሚያን መድበሎች ውስጥ መስፋፋቱን የብርሃኑ ገበየሁ ጥናት ይገልጻል፡፡
በዚህ መድብል ውስጥ በፍቅር፣ በፍልስፍናዊ እሳቤዎችና በትውልድ መሀል ባሉ ግጭቶች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ አዝናኝ ግጥሞች ተካተዋል፡፡ መድብሉ ከያዛቸው 26 ግጥሞች መሀል ግማሽ የሚሆኑት በፍቅር ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተፃፉ ወይም የፍቅር ጉዳይን በተወሰነ ደረጃ የሚያነሱ ናቸው፡፡ አብዛኛዎቹ ግጥሞች የተፃፉት ከ1937 እስከ 1950 ዓ.ም ድረስ ነው (መንግስቱ ለማ፣ 1955፡ መቅድም)፡፡

በዚህ መድብል ውስጥ የተካተቱ ብዙ አይረሴ እና ስሜት ንክር የፍቅር ግጥሞቻቸውም እንደ ልኂቅ ስራ በመወሰድ የስነ-ግጥምን ንድፈሀሳባዊ ባህሪያት ለማጥናትና ለመተንተን እንዲሁም በአስረጂነት ለማስተማር ዓላማዎች ውለዋል፡፡ ይህም ጥናት ያተኮረው የአማርኛ ስነግጥም ከፆታዊ የፍቅር ግጥሞች ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ በተዋወቀበት የመንግስቱ ለማ የግጥም መድብል ውስጥ በተካተቱት የፍቅር ግጥሞች ላይ ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አስፈላጊነት እና አምክንዮታዊነት

ፍቅር ሁለንተናዊነት ያለው የማንኛውም የሰው ልጅ መተሳሰሪያ ውልና የእለት ተዕለት ገጠመኝ እንደመሆኑ መጠን በርዕሰ ጉዳይነት መጠናት ያለበት ሰብዓዊ ፀጋ ነው፡፡ የማንኛውም ሰው የሰርክ የመነጋገሪያ ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን ወደ ኋላ መለስ ብሎ የፍቅር ግጥሞች መፃፍ ተጀመረበት ከተባለበት ዘመን ጀምሮ ስለፍቅር ማጥናት ለሀገራችን ይዘት ተኮር

የስነፅሁፍ እድገት፣ ለስነፅሁፋዊ የስነሂስ ጥናት፣ ለአንባብያን ስነፅሁፍን በአግባቡ የመረዳት ልማድ፣ በየዘመኑ የተነሱትን ገጣሚያን በስራቸው አማካይነት ለማጥናት፣ የስነፅሁፍን ታሪክና የዘመን መንፈስ በቅጡ ለመረዳት፣ ወዘተ. እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

ከርዕሰ ጉዳዩ አንፃር፣ የፍቅር፣ የስነወሲብና የስነፆታ ጉዳይ ራሱን እንደቻለ ዋነኛ ርዕሰ ጉዳይ በስነፅሁፍ ስራዎች ውስጥ እንዴት እንደተንፀባረቀ ያጠኑ ስራዎች በጣት የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ ይህም ጥናት በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በተደረጉ ጥናቶች ላይ ተጨማሪና አዲስ ዕውቀት የማምጣት እድሉ ከፍተኛ ነው፡፡

ከአንባብያን አንፃር፣ ከያኒው ከአንባቢያን ጋር የሚገናኘው በኪነጥበባዊ ስራዎቹ አማካኝነት ነው፡፡ ሁሉም አንባቢ ያነበበውን ሁሉ በትክክልና በአጋባቡ የመረዳት ተመሳሳይ አቅምና ችሎታ የለውም፡፡ በተለይ ስነግጥም እጅግ እምቅና ቅኔያዊ ባህሪያት ያሉት ጥበብ ነው፡፡ እምቁን ዘርዝሮ ድብቁን በማሳየት፣ የቅኔውን ምስጢር ፈቶ ሰምና ወርቁን በማሳየት ረገድ፣ እንደዚህ አይነቶቹ ስነሂሳዊና ሙያዊ ጥናቶች በገጣሚና በአንባቢ መካከል ድልድይ በመሆን ያገለግላል፡፡ ይህም ጥናት በደራሲውና በአንባቢው መካከል ያለውን ምናባዊ ርቀት በማቅረብ የገጣሚውን ስራዎች ይበልጥ እንዲገነዘብ የሚያደርግ ሚና ይጫወታል፡፡

ይህ ጥናት የስነፅሁፋዊ የዘመን መንፈስን ለማጥናት ለሚደረገው ጥረት የበኩሉን ግብዓት በማቅረብ ረገድ ሚናው ከፍ ያለ ነው፡፡ ስነፅሁፍ የየዘመኑን ማህበረሰብ ህሊናዊና ቁስ አካላዊ ታሪክ ቀርሶ በማኖር ረገድ ወደር የሌለው ሚና ይጫወታል፡፡ ይህም ጥናት ያተኮረው የኢትዮጵያ ስነግጥም ከስጋዊ ፍቅር ጋር ሊተዋወቅ በቻለበት ስራ ላይ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ስጋዊ ፍቅር ከሀገራችን ስነፅሁፍ ጋር በተዋወቀበት ዘመን የተንፀባረቁትን ኪናዊ መልኮች በተወሰነ ደረጃ በማሳየት የአማርኛ የስነግጥም ታሪክን በጥቅሉ ለማጥናት ለሚደረገው ጥረት ጥናቱ የበኩሉን አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ ከስነግጥም አንፃር በዘመን መንፈሶች ውስጥ የተነሱ ወሲባዊና ስነፆታዊ አተያዮችን ለማጥናት ወደፊት ለሚነሱ አጥኚዎች መነሻ የሚሆን ፍሬ ሀሳብ ያቀብላል፡፡

ይህ ጥናት በአገራችን ብዙ ባልተሰራበት የስነግጥም ጥናት ዘርፍ ባሉ ጥቂት ጥናቶች ላይ ተጨማሪ ንባብ በመሆን ከማገለግሉ በተጨማሪ በስነዘዴዎቹና በመተንተኛ ስልቶቹ አዲስ አቅጣጫ የማሳየት አቅምም አለው፡፡ በተለይም ለስነግጥም ፍካሬያዊ ጥናት መንገድ ጠራጊ በመሆን የበኩሉን ድርሻ በመወጣት ያገለግላል፡፡ በስነግጥም ዘርፍ በፍካሬ ልቡና የገጣሚያንን ምናብ ለመተንተንና የዘመን መንፈስን ለማውጣት ለሚደረጉ ጥረቶች መነሻ የሚሆን ሀሳብ ይሰጣል፡፡

### 1.3. የጥናቱ መላምትና ጥያቄዎች

ይህ ጥናት ይዞ የተነሳው በሀገራችን የስነግጥም ታሪክ ውስጥ የስጋዊ ፍቅርን እንደ አንድ ይዘት አካቶ ለመጀመሪያ ጊዜ ለህትመታ በበቃው የገጣሚው መድብል ውስጥ ወጥነት ያለውን የፍቅር ታሪክ የሚተርኩ ግጥሞች አሉ፤ በሚል መላምታዊ ጥርጣሬ ነው፡፡ ይህም መላ ምት የመነጨው በሁለት አበይት ምክንያቶች ነው፡፡ አንደኛው አጥኚው የስነ-ግጥምን ኮርስ በሚያስተምርበት ጊዜ ለማስተማሪያነት በተመረጡት የገጣሚው ግጥሞች መሀል በምልከታ ካገኘው የተወሰኑ ግጥሞች ዝምድና ይመነጫል፡፡ የተለያዩ የስነግጥም ይዘቶችን ለማስረዳት በዋሉ የማስተማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በተመረጡት አራት የገጣሚው የፍቅር ግጥሞች ላይ የቅርፅ፣ የይዘት፣ የአተራረክ፣ የገፀባህሪያት፣ ወዘተ. ተመሳስሎ ይታያል፡፡

ሁለተኛው ደግሞ መስፍን ዓለማየሁ የተባለ ጸሐፊ ስለገጣሚው ባቀረበው ፅሁፍ ውስጥ "በህፃንነታቸው ዝናሽ ትባል ከነበረችቷ ዘመዳቸው ጋር ሲጫወቱ ባደረባቸው አፍላጦናዊ ፍቅር ሳቢያ "ዘመናዊ የፍቅር ግጥሞችን" መጻፍ እንደጀመሩ ይታወቃል፡፡" (1988፡ 238) በማለት ከሰጠው አስተያየት ይመነጫል፡፡ ይህም አስተያየት ገጣሚው በፍቅር ግጥሞቻቸው ውስጥ ይህን ገጠመኛቸውን ቀርፀው ይሆን እንዴ? የሚል ጥርጣሬን ፈጥሯል፡፡ ከእነዚህ ሁለት ምክንያቶች

በመነሳት፣ ጥናቱ በመድብሉ ውስጥ ወጥነት ያለው የፍቅር ታሪክ የሚተርኩ ነጠላ የፍቅር ግጥሞች ሳይካተቱ አይቀሩም የሚል መላምት ይዞ ተነስቷል፡፡

ጥናቱም የሚከተሉትን ቁልፍ ጥያቄዎች በመመለስ የተነሳባቸውን መላ ምቶችና ጥርጣሬዎች ለማረጋገጥ ሞክሯል፡፡

1. በመድብሉ ውስጥ ከተካተቱት የፍቅር ግጥሞች መሀል ተያያዥነት ያለው የፍቅር ታሪክ የሚተርኩ ግጥሞች አሉ?
2. ወጥ ታሪክ የተገኘባቸው ግጥሞች እርስ በእርሳቸው የሚገናኙትና የሚዛመዱት እንዴት ነው?
3. በግጥሞቹ ውስጥ የተቀረፁት ተፈቃቃሪዎች የፍቅር ግንኙነት ከየት ተነስቶ የት ይደርሳል?

### 1.4. የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ ስነግጥማዊ ትንተና እና ፍከራ በማካሄድ በመድብሉ ውስጥ ወጥነት ያለው የፍቅር ታሪክ መተረኩን መመርመር ነው፡፡ ጥናቱ ጥቅል አላማውን ከግብ ያደረሰው የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች ደረጃ በደረጃ በመተግበር ነው፡፡

1. በመድበሉ ውስጥ የተካተቱ የፍቅር ግጥሞችን መለየትና መምረጥ፤
2. በመድብሉ ውስጥ በተካተቱት የፍቅር ግጥሞች መሀል ተያያዥነት ያለው የፍቅር ታሪክ መተረኩን መመርመር፤
3. ወጥ ታሪክ የተገኘባቸው የፍቅር ግጥሞች እርስ በእርሳቸው እንዴት እንደሚገናኙ በፍከራ መግለጥ፤
4. በግጥሞቹ ውስጥ የተቀረፁትን ተፈቃቃሪዎች፣ የፍቅር ግንኙነትና ታሪክ የሚያልፍባቸውን ሂደቶች መተረክ፤ የሚሉት ናቸው፡፡

## 2. ስነ-ዘዴ (Methods)

### 2.1. የጥናቱ አይነትና ንድፍ

ከርዕሰ ጉዳዩና ከዓላማዎቹ ባህሪያት አንፃር እንዲሁም ከመረጃዎቹና ከአጠቃላይ ስነዘዴያዊ ስልቶቹና ሂደቶቹ አንፃር ይህ ጥናት የሚመደበው ከአይነታዊ የምርምር ዘዴዎች (qualitative Research) መሀል ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በተመረጡ ስነፅሁፋዊ ስራዎች ላይ ስነሂሳዊ ምርመራ በማድረግ ስለሆነ ንድፈሀሳባዊና ስነዘዴያዊ ማዕቀፉ የተከተለው “ፈካሪ” (interpretative) እየተባለ የሚጠራውን የአጠናን ንድፍ ነው፡፡

ጥናቱ የተከተለው የፈካሪ ምርምር ስነዘዴያዊ ንድፍን በመሆኑ ያለፈባቸውም ሂደቶች የተቃኙት “ምን”፣ “እንዴት” እና “ለምን” የሚሉትን ጥያቄዎች ደረጃ በደረጃ በመመለስ ነው (Wiesner, 2022: 1)፡፡ በመጀመሪያም ጥናቱ “ምን” የሚለውን ጥያቄ ይዞ በመነሳት በስነፅሁፋዊው ስራ ውስጥ ባሉ አገላለፆች፣ ቃላት፣ ሙግቶች፣ ቅርፃዊ ቅጦች ወይም ድምፀቶችና ፅንሰሀሳቦች ላይ ንባብ ተኮር የይዘት ትንተና ላይ ያተኩራል።

ቀጥሎም በፈካሪ ጥናት ሁለተኛ የአጠናን ደረጃ መሰረት ጥናቱ በሚካሄድበት ንባብ ውስጥ በተካተቱ ቃላት፣ ሀረጋት፣ ትረካዎች፣ ምክንያታዊ ሙግቶች፣ ጭብጦች፣ ወይም ፅንሰሀሳቦችና ህሊናዊ ረቂቅ ምስሎች ላይ በማተኮር “እንዴት” እና “ለምን” (በምን አይነት ምክንያቶች) ፍቺዎችን ሊያዋቅሩ እንደቻሉ በመፈከር ምርምሯል (Wiesner, 2022: 1)።

## 2.2. የመረጃ ናሙና አመራረጥ

የዚህ ጥናት ዋነኛ ምንጭ "የግጥም ጉባዔ" በሚል ርዕስ በ1955 ዓ.ም ለሁለተኛ ጊዜ የታተመው፣ (የመጀመሪያው እትም 1950 ነው) የመንግስቱ ለማ የግጥም መድብል ነው፡፡ በዚህ መድብል ውስጥ የተካተቱት በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ 26 ነጠላ ግጥሞች ናቸው፡፡ ከነዚህ ግጥሞች መሀል ለጥናቱ የሚያስፈልጉት ግጥሞች የተመረጡት ዓላማና መስፈርት ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመከተል ነው፡፡ እንደ ዓላማም የተወሰደው ፍቅርን እንደ ጭብጥ ያነሱ ግጥሞች ላይ በማተኮር ነው፡፡ እንደመስፈርትም የተወሰዱት የፍቅር ግጥሞች ባህሪያት ናቸው፡፡

መስፈርት ተደርገው የተወሰዱትም ብርሃኑ ገበየሁ (2001፡ 179-180) *"ቀጥተኛነት፣ የስሜት ጥልቀትና ፍላት፣ ዜማዊነት እና ግላዊነት/እኔነት/"* በማለት የዘረዘራቸውን የፍቅር ግጥሞች አራት ዋና ዋና የወል ባህሪያት ነው፡፡

> *የፍቅር ግጥሞች **ቀጥተኛ** ናቸው ስንል፣ እንደ ዘፈን፣ እንደ ጸሎት ደራሹ ድምፅ /ተናጋሪው/ ተደራሹ/ዋን ገጸሰብ በግንባር ነው እሚያናግረው፣ "እኔ-አንተ/አንቺ" በማለት፡፡ በሌሎቹ የሌሪክ ንዑስ ዝርያዎች የተለመደ ቢሆንም፣ የፍቅር ግጥሞች እጅጉን ስሜት ንክር፣ በጣሙን ከጥልቅ ልቡና የሚፈሱ ናቸው፡፡ ስለዚህም አገላለጹ ስሜትን ይነዝራል፣ ወይም ልብን ያሞቃል. . .ከጥልቅ ነፍስ ውስጥ፣ በድንገት ፈንቅሎ የሚፈስ ኃይል ስሜት ሙዚቃዊና ዜማዊ ሲሆን የእንጉርጉሮ. . . የመባባት ወዘተ ስሜትን ያሰርጻል. . . . (2001፡179-180)*

በእነዚህ መስፈርቶች መሰረት ለጥናቱ የተመረጡት ከዚህ በተቻ ባሉት ርዕሶች የተዘረዘሩት 12 የፍቅር ግጥሞች ናቸው።

1. "የፍቅር ፍላፃ" (መንግስቱ ለማ፣ 25)
2. "ውኃ ማያጠፋው" (መንግስቱ ለማ፣ 1955፡ 22)
3. "እንዲያው ዝም" (መንግስቱ ለማ፣ 1955፡ 23)
4. "ጉድባይ" (መንግስቱ ለማ፣ 1955፡ 26)
5. "ሦስት ቀን ሲቀራት" (መንግስቱ ለማ፣ 1955፡ 28)
6. "ያገር ልጅ" (መንግስቱ ለማ፣ 1955፡ 33)
7. "በጠራ ጨረቃ" (መንግስቱ ለማ፣ 1955፡ 36)
8. "የወንድ ልጅ ያለህ" (መንግስቱ ለማ፣ 1955፡ 37)
9. "በገላጋይ" (መንግስቱ ለማ፣ 1955፡ 41)
10. "ተጣልተን ተኳርፈን" (መንግስቱ ለማ፣ 1955፡ 56)
11. "ሞትና መለየት" (መንግስቱ ለማ፣ 1955፡ 57)
12. "ጉድባይ ዳግማዊ" (መንግስቱ ለማ፣ 1955፡ 63)

የተለያዩ ይዘት ተኮር የትረካ፣ የፅንሰሀሳብና የትስስር ትንተናዎች በማካሄድ የጥናቱን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ አጠቃላይ መረጃዎች ከነዚህ 12 ግጥሞች ላይ ተሰብስበዋል፡፡

## 2.3. መተንተኛ ስልት

ጥናቱ በጥቅሉ የተከተለው የፈካሪ ምርምር ስነዘዴያዊ ንድፍን በመሆኑ የመረጃዎች ትንተናም የተካሄደው በፈካሪ የምርምር ዘዴ ውስጥ በሚካተቱ የተለያዩ ንዑሳን የትንተና ማዕቀፎች ውስጥ ነው፡፡ ትንተናውም የተደራጀው "ምን"፣ "እንዴት" እና "ለምን" የሚሉትን ጥያቄዎች ደረጃ በደረጃ ለመመለስ በሚያስችል መንገድ ነው (Wiesner, 2022: 1)፡፡ እነዚህንም ጥያቄዎች ለመመለስ በዋናነት ጥናቱ የተጠቀመው ንባብ ተኮር (Textual Analysis) እና ይዘት ተኮር (Content Analysis) የትንተና ስልቶችን ነው፡፡ በመጀመሪያም ጥናቱ "ምን" የሚለውን ጥያቄ ይዞ በመነሳት በመድብሉ ውስጥ ባሉ ግጥሞች፣ ርዕሰጉዳዮች፣ አሰነኛኘት፣ ቅርፅና ገጸ-ጽጉፍ፣ አገላለፆች፣ ቃላት፣ ሙግቶች፣ ቅርፃዊ ቅጦች ወይም ድምፀቶችና ፅንሰሀሳቦች፣ ወዘተ. ላይ ንባብ ተኮር ትንተና (Textual Analysis) ላይ አካሂዷል።

በንባብ ተኮር (Textual Analysis) ላይ ከተፃፉ ምርጥ ዘመናዊ መጻሕፍት አንዱ የሆነውንና Principles of Textual Criticism በሚል ርዕስ ያቀረበልን፣ James Thorpe እንደተናገረው፣ የንባብ ተኮር ስነሂስ ዋና ግብ የንባቡን ትክክለኛ ሀሳብ ገልጦ ማሳየት ወይም "ደራሲው ሊለው የፈለገውን ወይም ያሰበውን" ማዋቀር ነው። ይሁን እንጂ አንዳንድ ሰው እንደሚያስበው ይህንን ግብ ከዳር ማድረስ ቀላል አይደለም፡፡ ይህን አላማ ከግብ ማድረስ በተለይም ቆየት ባሉ ስራዎች ላይ ይበልጥ አስቸጋሪ እንደሚሆን የሚጠበቅ ቢሆንም ይህ አስቸጋሪነት በአሁን ዘመን ስራዎች ላይም ይገጥማል (Guerin et.al, 2011 17)።

ሆኖም፣ ንባብ ተኮር ጥናት የሚያካሂድ ሀያሲ መስጠት የሚገባው ስነ-ውበታዊ ፍርድ፣ የስራውን ንጥል ክፍሎች ብቻ ተመልክቶ ሳይሆን ሁሉንም ይዘቶች፣ ቃላዊ የሆኑ ንበቶችን ሁሉ ያካተተ ትንተና በስራው ላይ ማካሄድ አለበት፡፡ ሀያሲው ይህን የሚያደርገውና ወደ ፍከራው የሚያመራው በተቻለው አቅም ሂሳዊ ፍከራውንና ግምገማውን በሳይንሳዊ መንገዶች ላይ ለመመስረት ነው (Guerin et.al, 2011: 19)፡፡

በንባብ ተኮር ትንተና እና በጥልቅ ፈካሪ ስነሂስ መሀል ያለ ግንኙነት በህክምናው የቀዶ ጥገና ተምሳሌትነት ሊገለጽ ይችላል፡፡ በስነፅሁፋዊ ስራዎች የተለያዩ ክፍሎች ላይ የሚደረግ ንባብ ተኮር ትንተና በስራው ላይ ለሚደረጉ ሌሎች ተጨማሪ ጥናቶች መረጃዎችን ለማዘጋጀት ይረዳል (Guerin et.al, 2011: 19)፡፡

ቀጥሎም በፈካሪ ጥናት ሁለተኛ የአጠናን ደረጃ መሰረት ጥናቱ በሚካሄድበት ንባብ ውስጥ በተካተቱ ግጥሞች፣ ቃላት፣ ሀረጋት፣ ትረካዎች፣ ምክንያታዊ ሙግቶች፣ ጭብጦች፣ ወይም ፅንሰሀሳቦችና ህሊናዊ ረቂቅ ምስሎች ላይ በማተኮር “እንዴት” እና “ለምን” (በምን አይነት ምክንያቶች) (Wiesner, 2022: 1) ፍቺዎችን ሊያዋቅሩ እንደቻሉ የይዘት ትንተና (Content Analysis) በማካሄድና በመፈከር ምርምሯል።

የይዘት ትንተና (Content Analysis) ላይ በመረጃዎች ውስጥ በቀጥታ ተገልፀው እና ተሸሽገው የሚገኙ ጽንሰ-ሐሳቦችን ግንኙነት ይመረምራል (Abrams, 1991; Carpenter, 2002)። ይዘት ተኮር ትንተና በስራው ውስጥ የሚገኙ ተተኳሪ ድርጊቶች፣ ሁነቶች፣ ዘይቤዎች፣ ምስሎች፣ ቃላትና ሀረጋት እንዲሁም ምልክቶችና ቅርፆች፣ በተሰበሰቡት መረጃዎች ውስጥ የሚያመለክቱዋቸውን ይዘቶች፣ አቢይ ርዕሰ ጉዳዮች፣ ጽንሰ-ሐሳቦችና ፍቺዎችን በመገምገም ይጀምራል፡፡ ቀጥሎም፣ ይህም ግምገማ ከፅሁፉ ይዘቶች ውስጥ ሰፋ ያሉ ፍከራዎችን ለማካሄድ የሚያገለግሉ ጭብጦችን ያወጣል (Carpenter, 2002)። የዚህ ሂደት አላማም የመረጃዎቹን ዋነኛ ጽንሰ-ሐሳቦች እና ፍቺዎችን መሰብሰብ እና በመካከላቸው ያሉትን ግንኙነቶች መተንተን ነው።

የይዘት ትንተና ብዙውን ጊዜ የሚካሄደው የተሰበሰቡ መረጃዎችን በሁለት ማዕቀፎች ውስጥ በማካተት ነው፤ በፅንሰሀሳብ እና በትስስር ማዕቀፎች ውስጥ፡፡ እነዚህም ማዕቀፎች በዋናነት የሚለያዩት በትከረታቸው ነው እንጂ አንዱ በአንዱ ውስጥ ብዙውን ጊዜ ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡

ጽንሰ-ሐሳባዊ ትንተና (Conceptual Analysis) በመረጃዎች ውስጥ ያሉ ዋነኛ ጽንሰ-ሐሳቦችን የሚደግፉ ንባቦችና ክፍሎችን በመለየት ላይ ያተኩራል (Abrams, 1991; Carpenter, 2002)። ይህ ዘዴ በተሰበሰቡ መረጃዎች ውስጥ ባሉ ግልጽ ይዘቶች ላይ ያተኩራል፤ እንዲሁም በመረጃዎች ይዘት እና በሚጠኑት ዋነኛ ፅንሰሀሳቦች መሀል ያለን ቀጥተኛ ግንኙነት ለመፍጠር ያስችላል፡፡

የትስስር ትንተና (Relational Analysis) የተካሄደው በጽንሰ-ሐሳባዊ ትንተና ውስጥ የተገኙ መረጃዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። በአጠቃላይ መረጃዎች ውስጥ የተገኙ ጽንሰ-ሐሳቦችና ፍቺዎች ከሌሎች ተዛማጅ ርዕሰ ጉዳዮች

ጋር እንዴት እንደሚዛመዱ ይመረምራል (Carpenter, 2002)። በሌላ አነጋገር፣ በግጥሞቹ ውስጥ በቀጥታ በተገኙ ግልፅ መረጃዎች እና በአውዶች ውስጥ ተሸሽገው በተገኙ ድብቅ ጽንሰ-ሐሳቦች መካከል ያለውን ግንኙነት ይመረምራል። በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ የተካሄደ ትንትና ውስጥ ልብ ሊባል የሚገባው ነገር አለ፡፡ ይህ ትንተና የተካሄደው በፅንሰሀሳቦች መካከል አስፈላጊ የሆነ ጉልህ ዝምድና በመፈለግና ከነዚህ ግንኙነቶች የመነጩ ፍቺዎችን በማውጣት እንጂ ብቻቸውን በቆሙ ፅንሰሀሳቦች ላይ በማተኮረ አይደለም (Abrams, 1991)።

እነዚህን ስልቶች በመጠቀም በቅድሚያ ተደጋጋሚ ምልከታ በመድብሉ ውስጥ በተካተቱት ግጥሞች ላይ በማካሄድ 12 የፍቅር ግጥሞች ተለይተዋል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥም የተመረጡት ግጥሞች እርስ በእርስ ትስስር እንዳላቸውና ስሜት ሊሰጥ በሚችል የጊዜ ቀደም ተከተል ሊያደራጃቸው የሚያስችል አወቃቀር እንዳላቸው የሚጠቁሙ መረጃዎች ተገኝተዋል፡፡

ቀጥሎም በቀዳሚው ሂደታዊ ደረጃ ስሜት ሊሰጡ በሚያስችላቸው የተሰናሰለ አደረጃጀት በተዋቀሩት ግጥሞች ውስጥ የተገኙ ተደጋጋሚ ትዕምርቶችና ምስሎች ለማብራራትና የያዙትን ትዕምርታዊ ውክልና ለመረዳት (Schmitz, 2007: 198) የሚያስችል ይዘት ተኮር የትስስር ትንተና ተደርጓል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥም ተፈቃሪዋና አፍቃሪው ወደ ፍቅር የገቡባቸውን፣ በፍቅር የቆዩባቸውን እና የፍቅራቸውን የመጨረሻ እጣ ፈንታ ሊያሳዩ በሚችሉባቸው ቅደም ተከተላዊ መንገዶች ተደራጅተዋል፡፡

በመጨረሻም የጊዜ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው የተፋቃሪዎቹን የፍቅር ታሪክ ሲተርኩ የተገኙ ስድስት ግጥሞች ለአብነት ያህል ተመርጠው በጥናቱ የፍከራ ክፍል ውስጥ በቀጥታ ተካተዋል፡፡ እነዚህም "የፍቅር ፍላፃ" (መንግስቱ ለማ፣ 1955፡ 25)፣ "ያገር ልጅ" (መንግስቱ ለማ፣ 1955፡ 33) ፣ "እንዲያው ዝም" (መንግስቱ ለማ፣ 1955፡ 23) ፣ "ውኃ ማያጠፋው" (መንግስቱ ለማ፣ 1955፡ 22) ፣ "ተጣልተን ተኳርፈን" (መንግስቱ ለማ፣ 1955፡ 56) እና "ጉድባይ" (መንግስቱ ለማ፣ 1955፡ 26) በሚሉት ርዕሶች የቀረቡት የፍቅር ግጥሞች ናቸው፡፡

## 3. የመረጃዎች ትንተና እና ውጤት (Results and Discussion)

በጥናቱ ጥያቄዎችና አላማዎች መሰረት፣ ይህ ክፍል፣ ተያያዥነትና ወጥነት ያለው የፍቅር ታሪክ በየትኞቹ የፍቅር ግጥሞች ውስጥ እንደተተረከ፤ ወጥ ታሪክ የተገኘባቸው የፍቅር ግጥሞች እርስ በእርሳቸው እንዴት እንደሚገናኙ፤ በተለያዩ ነጠላ የፍቅር ግጥሞች ውስጥ የተተረከው የፍቅር ታሪክ አነሳስ፣ እድገትና መጨረሻ በምን አይነት ሂደቶች ውስጥ እንዴትና በምን ምክንያቶች እንዳለፈ በሚገልጥ ፍከራ ውስጥ የጥናቱ ውጤቶች ይቀርባሉ፡፡

ከግጥሞቹ ውስጥ በተገኙት ቅደም ተከተላዊ ቅጦች መሰረት የፍቅረኛሞቹ የፍቅር ታሪክ "ውዳሴ - የፍቅር ዋዜማ"፣ "ጥበቃ - የፍቅር ማግስት" እና "ስንብት - የፍቅር ፍፃሜ" የሚሉ ርዕሶች በተሰጣቸው ምዕራፎች ውስጥ እየተፈከሩ ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

### 3.1. ውዳሴ - የፍቅር ዋዜማ

ለመጀመሪያ ጊዜ ተፈቃሪዋ ልቡናዊ ቅርፅ እና ይዘት ተሰጥቷት ስትቀረፅ፣ ከዛም በፍቅሯ ፍላፃ ተራኪውን ስትነድፈውና ስትፈቅር፣ የሚያሳየውን ምዕራፍ የምናገኘው 'ያገር ልጅ' (33) እና 'የፍቅር ፍላፃ' (25) በሚሉ ርዕሶች በቀረቡት ግጥሞች ውስጥ ነው፡፡ ይህ ምዕራፍ የተናጋሪውን ወደ ፍቅር የመንደርደሪያ ሂደታዊ ታሪክ ያቀርብልናል፡፡

## 1. የፍቅር ፍላፃ

ፍላፃ ንብ ራሷን ለመካላከል የምትናደፍበት መርዛማ ንጥረ ነገር ነው፡፡ አካል በዚህ መርዛማ ንጥረ ነገር ከተነደፈ የማቃጠል፣ የመለብለብ ስሜት ይፈጠርበታል፡፡ ይህ መርዛማ ነገር የፍቅር ሲሆንስ? ርዕሱ የተፈቃሪዋን የፍቅር መንደፊያ እና በፍቅሯ የተነደፈ ሰው የሚሆነውን የሚያሳይ ይመስላል፡፡

**የፍቅር ፍላፃ**

ፈረንሳይ እንግሊዝ ጀርመን ጣልያን
ስትጽፍ ስትናገር አይዛት አፋ[1]ን
በርኔጣዋ፣ ሠፌድ በፓሪሱ ቄንጥ
የጫማ ተረከዝ ስንዝር የሚበልጥ
ሥልጡን የተማረች፣ የሠለጠነች…
ብለው ሲወድሱሽ ሲሻሙሽ ሰዎች፤
…………
(መንግስቱ ለማ፣ 25)

የተፈቃሪዋ በፍቅር የመንደፊያ ፍላፃ የተገለጸው በግጥሙ የመጀመሪያ አርኬ ውስጥ ነው፡፡ የግጥሙ ተናጋሪ ሰዎች ተፈቃሪዋን የሚወዷት በዋነኝነት በቋንቋ ችሎታዋ እና በስልጡንነቷ ነው፤ የሚል ይመስላል፡፡ የቋንቋ ችሎታዋንም ሆነ ስልጣኔዋን በተፈጥሮ ያገኘችው ሳይሆን በትምህርት ያዳበረችው ነው፡፡ የስንኞቹን ክፍሎች እስኪ አንድ በአንድ በመፈከር የተፈቃሪዋን የፍቅር መንደፊያ እንመልከት፡፡

ፈረንሳይ እንግሊዝ ጀርመን ጣልያን
ስትጽፍ ስትናገር <u>አይዛት አፏን</u>
…………

የግጥሙን የመጀመሪያ ቤት መምቻ ሀረግ (‘አይዛት አፏን’) ይዞን የሁለቱን ስንኞች ሀሳብ ብንመረምር በሁለት መንገዶች ልንፈክረው እንችላለን፡፡ ‘አፍ መያዝ’ ሁለት የተለያዩ ፍችዎችን የያዘ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፡፡ በአንድ በኩል ‘‘አፉን ይይዘዋል’’፣ ‘‘አፉን ያዝ ያደርገዋል’’ ስንል አንድ ሰው ሁለተኛ ቋንቋውን በትክክል መናገር አይችልም፤ ሀሳቡን በሁለተኛ ቋንቋው እንደልቡ መግለጽ አይችልም ማለታችን ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ‘‘አፉን አስያዘው’’፣ ‘‘አፍህን ያዝ’’፣ ‘‘አፉ ተያዘ’’ ስንል፣ እንዳይናገር ተገደደ፤ ሀሳቡን በንግግሩ በነፃ እንዳይገልፅ ፈራ፤ በአስገዳጅ ሀይል መናገር ተሳነው፤ የሚሉ ፍችዎችን ያመጣል፡፡

‘አይዛት አፏን’ የሚለውን ሀረግ ቀድሞት ከመጣው ‘ስትጽፍ ስትናገር’ ከሚለው ሀረግ ጋር ስናያይዘው የተፈቃሪዋን የመጻፍ እና የመናገር ከሂሎች የላቀ ብቃት ይገልጻል፡፡ በመጀመሪያው ስንኝ የተዘረዘሩት የአገር ስሞችም የሚያመለክቱት ተፈቃሪዋ በብቃት የምትጽፍባቸውንና የምትናገራቸውን ሁለተኛ ቋንቋዎች ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በመጀመሪያው ስንኝ የተዘረዘሩት የአገር ስሞች ከግጥሙ የመጀመሪያ አርኬ አውድ አንፃር ከቋንቋ ውጪ ስልጣኔንም ያመለክታሉ፡፡ ‘ፈረንሳይ እንግሊዝ ጀርመን ጣሊያን’ የሚሉት የስፍራ ስሞች ከተፈቃሪዋ ጋር በተያያዘ ማደሪያ የሆኑት ለስልጣኔም ነው፡፡ በገሀድ እንደሚታወቀውም እነዚህ አገሮች በስልጣኔያቸው የገነኑ ብቻ ሳይሆኑ ከአለማችን ሀያላን አገሮች መካከል የመጀመሪያዎቹ ናቸው፤ በተለይም ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በፊት፡፡

ከነዚህ ገናን አገሮች ስልጣኔ እና ሀያልነት ጋር ‘አይዛት አፏን’ የሚለውን ሀረግ ስናናብብ የምናገኘው የጥምር ቃሉን ሁለተኛ ፍች ነው፡፡ ተፈቃሪዋ የፈለገችውን ብትጽፍም ሆነ ብትናገር የተጠቀሱት አገሮች ስልጣኔና ሀይል አፏን

[1] ግጥሙ የተወሰደበት መድበል ‘አፋን’ ብሎ ነው ያስቀመጠው፡፡ ከግጥሙ አውድ አንፃር ‘አፏን’ ለማለት ይመስላል፡፡ /ፏ/ ተብላ ልትጻፍ የተፈለገችው ፊደል /ፋ/ ተብላ የተጻፈቸው በአርትዖት ችግር ይመስላል፡፡ ስለዚህ ይህ ቃል የተፈከረው /አፏን/ በሚለው ማስተካከያ ነው፡፡

ሊያዘጋት አይችልም፤ የሚል ይመስላል፡፡ አገራቱም በተናጥል በነጠላ ሰረዝ አልተዘረዘሩም፤ የአንድ ሰው ስም እስከ ቅድመ አያቱ ድረስ በሚጻፍበት ቅርፅ ነው፤ የቀረበው፡፡ 'አይዛት' በሚለው ቃል ድርጊት ፈፃሚው ነጠላ ቁጥር ያለው ባለቤት ነው፡፡ በዝርዝር ቢቀርቡም በሦስተኛው እና በአራተኛው አገር ስም መካከል 'እና' የሚል አያያዥ ቃል ይገባ ነበር፡፡ ከዚህ እንደምንረዳው አገራቱ በአንድ ተጨፍልቀዋል፡፡ ይህም ቅርፃዊ ፍከራ ተፈቃሪዋ ስለፈለገችው ብትጽፍ፣ ስለፈለገችው ብትናገር አገራቱ በተናጠል አይደለም በአንድነት ቢመጡ እንኳን ጫፏን ሊነኳት አይችሉም የሚል አፅንኦታዊ ፍች ያመጣል፡፡ ይህም አፅንኦት ተፈቃሪዋን ከአገራቱ የመጻፍ እና የመናገር ሀያል መብት ጋር የሚያወዳድር፣ የሚያፎካክር፣ እንዲሁም የሚያስበልጥ ይመስላል፡፡

'አይዛት አፏን' የሚለውን ሀረግ አሁንም ከሁለቱም ፍችዎቹ አንፃር መልሰን ብናየው ከተፈቃሪዋ የቋንቋ ክሂሎች መላቅ ይልቅ ፍችው የሚያደላው ለተፈቃሪዋ ስልጡንነት እና ከቋንቋ ጋር ለተያያዘ ሀያልነት ነው፡፡ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች (የማድመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብ እና የመጻፍ ክሂሎች) ውስጥ ሁለተኛ ቋንቋን ያጠና ሰው አፉን ያዝ እንደሚያደርገው መዝነን የምናረጋግጠው በሁለተኛው ቋንቋ ሲናገር እና በዛው ቋንቋ የተጻፉ ጽሁፎችን ሲያነብ ሰምተን ነው፡፡ ተፈቃሪዋ አፏን ያዝ እንደማያደርጋት የተነገረን የሁለተኛ ቋንቋዎቿን ጽሑፎች ስታነብ አይደለም፤ ስትጽፍባቸው እንጂ፡፡ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ብቻ ሳይሆን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ከአራቱ ክሂሎች የሚከብደው እና የላቀ ችሎታንም የሚጠይቀው የመጻፍ ክሂል ነው፡፡ ሁለተኛ ቋንቋን በብቃት መናገር መቻልም የሚገልፀው ከመጀመሪያ ተናጋሪው እኩል መናገር መቻልን ብቻ ሳይሆን የዛን ቋንቋ ባህልና እምነትም በሚገባ ማወቅን ጭምር ነው፡፡ ምናልባትም ሁለተኛውን ቋንቋ በብቃት የሚናገረው ሰው ከሚናገረው ቋንቋ ባለቤት ጋር አብሮ መኖርም ሊጠበቅበት ይችላል፡፡ በጥቅሉ ተፈቃሪዋ ከመጤዎቹ ቋንቋዎች ሁለት ክሂሎች ጋር የተያያዘቸው ክሂሎቹ በቀጥታ ለሚያሳዩት የችሎታ ማሳያ ብቃት ሳይሆን የክሂሎቹ ማደሪያ የሆኑት ጽሑፍ እና ንግግር ከያዙት ረቂቅ ፅንሰሀሳቦች ጋር ነው፡፡

ጽሑፍ እንደሚታወቀው የሰው ልጅ ስልጣኔውን ቀርሶ የሚያኖርበት ታላቅ ቅርሱ ነው፡፡ ለዘመናዊ ስልጣኔውም የጀርባ አጥንት የሆነውን 'ትምህርት' የሚቀርስበት እና በማሄጃነት የሚጠቀምበት ታላቅ ፈጠራው ነው፡፡ ጽሑፍ የትምህርትም ሆነ ሰብአዊ የስልጣኔ ውጤቶችን ለዘመናት ከትውልድ ወደ ትውልድ፣ ከስፍራ ስፍራ ሲያሸጋግር የኖረ እና የሚኖር መቅረሻ ሰነድ ነው፡፡ ንግግርም የተለየ ጥበብን የሚጠይቅ እና በሌሎች ዘንድ የላቀ ተሰሚነትን የሚያጎናጽፍ፣ ከጥንት ጀምሮ በተለየ ትኩረት ሲጠና የኖረ የተግባቦት መሳሪያ ነው፡፡

በግጥሙ የተጠቀሱት አገሮች የአለማችንን ህዝቦች ቋንቋዎች በማጥናትና በጽሑፍ ቀርሶ በማኖር ረገድ ተወዳዳሪ የላቸውም፡፡ የአገራችን አያሌ ጥንታዊ ጽሑፎችም በነዚህ አገሮች ሙዚየሞች ውስጥ እንደሚገኙ ይታወቃል፡፡ እነዚህ አገሮች በጥቅሉ ለጽሑፍ የተለየ ስሱነት አላቸው፡፡ ርዕዮተ አለማቸውንም ሆነ ትምህርታቸውን በአለም ላይ በማስፋፋት አለሙን ሁሉ በዕሳቤያቸውና ባህላቸው መዳፍ ውስጥ ያስገቡት ባብዛኛው በጽሑፋቸው ነው፤ ማለት ይቻላል፡፡ የጽሑፍ ሀብታቸውም ሆነ ጽሑፋቸው የስልጣኔያቸው መሰረት በመሆን የተጫወተው ሚና እና አሁን ድረስ በአላማችን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ላይ የሚጫወተው ሚና ይኼ ነው ተብሎ የሚገመት አይደለም፡፡ በጽሁፋቸው ብቻ የእነዚህ አገሮች የበላይነት እና ሀያልነት እንዴት እንደሚንፀባረቅ ማሳየት ይቻላል፡፡ ጽሑፍ ለአገሮቹ ከተጫወታቸው ሚናዎች አንፃር የተፈቃሪዋን የመጻፍ ክሂል ከጠባብ ግላዊ ክሂልነቱ ባሻገር ተፈቃሪዋን በስልጣኔዋ እና በትምህርቷ ለማፎካከር ሆን ተብሎ የገባ ስልታዊ ማንፀሪያ ይመስላል፡፡ የላቀ ንግግሯም የተወዳደረው፣ የተጠቀሱት አገሮች በአለማችን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ካላቸው የላቀ ተሰሚነት አንፃር ይመስላል፡፡

እዚህ መደምደሚያ ላይ እንድንደርስ የሚያደርገን የተጠቀሱት አገሮች በቀጣዮቹ ስንኞች በተፈቃሪዋ የተማረችነት እና የሰለጠነች ምሰላዎች ውስጥ የተነሱበት አውድ ነው፡፡ 'ሥልጡን የተማረች፣ የሠለጠነች…' በሚለው ስንኝ ውስጥ የገቡት ነጠብጣቦች ፍከራችንን በዚህ መንገድ ለጥጠን እንድንመለከተው የሚያስችልም ፍንጭ ስላቀረቡልን ነው፡፡

……………
ባርኔጣዋ፣ ሡፌድ በፓሪሱ ቄንጥ
የጫማ ተረከዝ ስንዝር የሚበልጥ
……………

ተፈቃሪዋ በነዚህ ስንኞች ውስጥ የምትታየው እናቷን በኢትዮጵያዊ ሻሽ ሽብ አድርጋ እና 'ኮንጎ' እየተባለ የሚጠራውን ፕላስቲክ ጫማ ተጫምታ አይደለም፡፡ የተጠቀሱት አገሮች ሴቶች በሚያጌጡባቸው አልባሳት መካከል ሆና ነው የምትታየው፡፡ የተጠቀሱት ምዕራባዊ ማጌጫዎች የዋሉት ከተፈቃሪዋ እናት በላይ እና ከእግሮቿ በታች ነው፡፡ ከእናቷ በላይ የዋለው ባርኔጣ ሰፊ ነው፡፡ ባርኔጣውም በለዋጭ ዘይቤ የተመሰለው በሡፌድ ነው፡፡ ሡፌድም ለባርኔጣው ያዋሰው ስፋቱን እና ጎበብ ያለ ቅርፁን ይመስላል፡፡ ባርኔጣው የተዘጋጀው በፓሪስ ቄንጥ ነው፡፡ ቄንጥ ደግሞ ፈጠራ የታከለበት የሚማርክ ጥበባዊ አሰራርን ወይም አከዋወንን የሚያመለክት ቃል ነው፡፡ ፓሪስ ደግሞ በተለይ በአርኪቴክቸሩ ጥበብ እና በተለያዩ ኪነጥበባዊ ቅርሶች የተንቆጠቆጠች የአለማችን ቁጥር አንድ ከተማ ነች፡፡ በተፈቃሪዋ እናት ላይ ሰፋ ጎበብ ብሎ የሚታየው ባርኔጣ የአለማችን የላቀ ጥበብ ያረፈበት ቁስ ነው፡፡ ይህ በላቀ ማራኪ ጥበብ የተሰራ ቄንጠኛ እደጥበብ (ባርኔጣው) ከተመሰለበት አገራዊ መሰሉ(ሡፌዱ) አገልግሎት አንፃር ብንፈክረው፡- ማንፈሻ፤ ማበጠሪያ፤ ፍሬውን ከገለባው፣ አስፈላጊውን ከቁሻሻው መለያ ይሆናል፡፡ ሡፌዱ ለባርኔጣው ያዋሰው ስፋት እና ቅርፁን ብቻ ሳይሆን ተግባሩንም ይሆናል ማለት ነው፡፡

በፓሪስ የላቀ ጥበብ በቄንጥ የተንቆጠቆጠው ባርኔጣ ፋይዳውን ከአገራችን መሰሉ፣ ከሡፌድ፣ ሲወስድ ለተፈቃሪዋ ማጌጫነቱ ብቻ ሳይሆን አገልግሎቱም ይጨመርላታል፡፡ ተፈቃሪዋ እናት ላይ የተደረገው ባርኔጣ እብቁን ከፍሬው፣ ከፉን ከደጉ፣ ጎጂውን ከጠቃሚው አንፍሳና አበጥራ እንድትለይበት ከሰለጠኑት አገሮች ያመጣችው ወይም የመጣላት ሰፊ የጥበብ አክሊል ይሆናል ማለት እንችላለን፡፡ እንዲያ ካልን ባርኔጣው በተቀመጠበት ተገቢ ስፍራው እና በአገራችን ባህላዊ የእደጥበብ ምሰላው፣ መጠቅ ሰፋ ያለ ተግባር ያለው የጥበብ አክሊል በተፈቃሪዋ ራስ ላይ አውሏል፡፡

ጫማው ደግሞ በርዝመቱ ተፈቃሪዋን ካለችበት ዝቅተኛ ስፍራ ከፍ ያደርጋታል፡፡ ጫማው 'ሂል' በመባል የሚታወቀው የምዕራባውያን ወይዛዝርት መጫሚያ ነው፡፡ የተፈቃሪዋን የኋላ የእግር ክፍል ወይም ተረከዟን ከፍ የሚያደርግ ጉርሻ ያለው ጫማ ነው፡፡ ከሌሎች ጫማዎች የሚለየውም አካል ሚዛኑን ጠብቆ በሚያርፍበት የተረከዝ ክፍል ላይ በሚጨመርለት ቀጠን፣ ረዘም ያለ መርገጫው ነው፡፡ በግጥሙ የመጀመሪያ ስንኝ የተዘረዘሩትን አገሮች እዚህ ጋ ደግሞ በወይዛዝርቶቻቸው ብንወክላቸው፣ ጫማው፣ ተፈቃሪዋን እንደምዕራባውያኑ ወይዛዝርት ከፍ፣ ረዘም አድርጎ በቁመት ያወዳድራታል፡፡

በተፈቃሪዋ ራስ ላይ የዋለውን ባርኔጣ በሰፊ የጥበብ አክሊል ከመሰልነው፣ አካሏ ሚዛኑን ጠብቆ እንዲቆም በሚያስችለው ተረከዟ ላይ የተጨመረውን ረዘም ያለ 'ታኮ' የጥበብም ሆነ የስልጣኔ መሰረት በሆነው 'ትምህርት' መስለን መመልከት እንችላለን፡፡ 'ታኮ'ው የተፈቃሪዋ አካል ሚዛኑን ጠብቆ እንዲቆም በሚያስችለው መሰረት ላይ የታከለ ማርዘሚያ፣ ማሳደጊያ በመሆኑ ተረከዘ ረጅም ጫማው የተፈቃሪዋ ትምህርት ነው፡፡ የፍቅር መንደፊያዋም በጫማው ምሰላ የቆመችበት መሰረት 'ትምህርቷ' ነው፡፡

………….
ሥልጡን የተማረች፣ የሠለጠነች ...
ብለው ሲወድሱሽ ሲሻሙሽ ሠዎች
………….

ከላይ ለማየት እንደሞከርነው የዚህ ግጥም ተናጋሪ በስነግጥማዊ ምሰላው ተፈቃሪዋን ያቀረበው ከአራት ገናን የአውሮፓ አገሮች ጋር አያይዞ ነው፡፡ አገሮቹ በስመሀዳሪ ዘይቤያዊ ምሰላቸው ለተፈቃሪዋ የስልጣኔ መሰረቱን በትምህርት ያፀና ጥበብን፣ የበላይነት፣ የተሰሚነት እና በራስ የመተማመን ስሜትን አውሰዋል፡፡ የቆመችበት መሰረትም ከነዚህ ስልጡን

አገሮች ወይዛዝርት በተወሰደ መጫሚያ ከፍ ረዘም ብሏል፡፡ አናቷ ላይ የተደፋላት የጥበብ አክሊልም ከሰለጠኑት አገሮች መካከል በስነጥበባዊ ሀብቱ ላቅ ብሎ በሚታየው ከተማ ጥበብ የተሰራው ባርኔጣ አገራዊ ፋይዳና ጥበብ ተጨምሮበታል፡፡ ተፈቃሪዋ ከተጠቀሱት አገሮች ወይዛዝርት ጋር እኩል ሁና የምትወዳደር፣ የምትፎካከር ትመስላለች፡፡ በምዕራባውያኑ ባርኔጣ እና ጫማ መካከል ያለው አካሏ ግን አይታይም፡፡

ተፈቃሪዋ በጡቶቿ፣ በዳሌዋ፣ በአፍንጫዋ፣ በፀጉሯ፣ ወዘተ. አፍቃሪዎቿን በፍቅር ፍላፃዋ ስትነድፍ አትታይም፡፡ ሁሉኑም ወዳጆቿን በፍቅሯ ነድፋ እንዲሻሟት የምታደርጋቸው በጥልቅ ትምህርቷ እና በስልጣኔዋ ብቻ ነው፡፡ በስልጡንነቷ እና በተማረችነቷ የተማረኩላት ብዙዎች ተፈቃሪዋን ለማግባት ሲለፉ ይታያሉ፡፡ በዘመናዊነቱም ሆነ በጥሪትና ሀብቱ ሊያባብላት የሞከረ አይሳካለትም፤ በሀይልና በስልጣኑም ስጦታ አይማርካትም፡፡

..........
አንዱ በቢዩክ መጥቶ ''እንውጣ'' ሲልሽ
በሼቭሮሌት አንዱ ሲያንሸረሽርሽ
መዳብ ያለው ብሩን፤ ወርቅ ያለው ዕንቁን
የራስ አክሊል ያለው ሲሰጥሽ ዘውዱን
..........

በእጁ ያለውን ብቻ ሳይሆን የሌለውንም እንኳን ሊሰጣት የሞከረ ተፈቃሪዋን አያገኛትም፡፡ ሙገሳ የሚያውቅ እና ከምሩ የወደዳት ግን ባያገኛት እንኳን ይሾማል፤ ይሸለማል፡፡

.........
ማሞገስ የሚያውቅም፤ ሲዘፈን ያንችን ስም
ወድሻለሁ ያለሽ ሲሸለም ሲሾም፤
.........

ተፈቃሪዋ የምትነድፈው ባለትዳር እና የልጆች አባትንም ጭምር ነው፡፡ ራሷ ላይ ያለው ጥበባዊ ማንፈሻ ግን እያበጠረ፣ እያንገዋለለ ከሷ ያርቃቸዋል፡፡ ይህንን ተፈጥሮዋን የተረዳው ፈላስፋው የግጥሙ ተናጋሪ ግን በፍቅሯ ቢነደፍም አመቺ ጊዜን አድፍጦ በትዕግስት ይጠብቃል፤ ሊያገባት፡፡

............
እንዳላየ ዓይቼ
ሰምቼ እንዳልሰማ
በፈላስፋ ትዕግስት ስቀር ሳልሻማ፣
በኒያ ሁሉ ልብሽ ቢጨክን ቢጠም፤
ከንፈርሽ ከሌላ ሰው ከንፈር ባይገጥም
ፍቅርሽ ተፈትኖ በገንዘብ በእሳቱ
ታወቀ ማለት ነው፤ ጥሩ ወርቅነቱ፡፡

በምዕራባውያኑ ባርኔጣ እና መጫሚያ መካከል አካሏ የሌለው ተፈቃሪ ሴት አካልና መልክ ይዛ የምትገኘው በሚከተለው ግጥም ውስጥ ነው፡፡

## 2. ያገር ልጅ

በላይኛው ግጥም ቁንጠኛ ባርኔጣ እና ተረከዘ ረጅም መጫሚያ መካከል ያለውን ባዶ ስፍራ የምትሞላው፣ የዚህ ግጥም ተፈቃሪ ትመስላለች፡፡ ወዳጆቿን ሁሉ አሻፈረኝ ያለችው ተፈቃሪ ሙሉ አካልም የሚታየው በዚህ ግጥም ውስጥ ነው፡፡ በተፈቃሪዋ ቅደም ተከተላዊ የታሪክ አወቃቀር ውስጥ ቀድሞ የሚመጣው ምስሏ በዚህ ግጥም የቀረበችበት አካላዊ ማንነቷ ነው፡፡

አካሄድሽ ይምጣ
አረማመድሽ
ጥርስ አገላለጥሽ

ከከንፈሮችሽ
ትሕትናሽ አይለይ ከቅንነትሽ፡፡
አንገትሽ ብርሌ
ወይኒቱ
ማር ነሽ፡፡

እቀፉኝ ቢል እንኳ
ደግፉኝ አይልም
ምርኩዝ የማያሻው
አቋቋመ መልካም
ወጣቱ ጡትሽ፡፡
ጨዋታ አዘውታሪ ቀበጥ ነው ዳሌሽ፡፡

ተረከዘ ሎሚ ጫማ የሌለሽ
ነይልኝ ያገር ልጅ
አውቃለሁ
አለሽ፡፡
(መንግስቱ ለማ፣ 33)

ተናጋሪው በ'የፍቅር ፍላፃ' ትረካው ውስጥ ለተፈቃሪዋ እግሮችና አናት ላደረገላት ባርኔጣ እና መጫሚያ ምክንያት የተገለጸው እዚህኛው ውስጥ ነው፡፡ ጡቷ ግን በዚህ ግጥም እንደምናየው ጡት ማስያዣ አያስፈልገውም፡፡ ድጋፍ የማያሻው ተፈጥሯዊ ውበቱን እንደጠበቀ ቀጥ ብሎ ይታያል፡፡

…

እቀፉኝ ቢል እንኳ
ደግፉኝ አይልም
ምርኩዝ የማያሻው
አቋቋመ መልካም
ወጣቱ ጡትሽ፡፡

…

ጥርሷ፣ ከንፈሯ፣ እንገቷ፣ ወዘተ. በጥቅሉ አካላዊ ውበቷ በራሱ ሌላ መድመቂያ (የከንፈር ቀለም፣ የአንገት ሀብል፣ ወዘተ.) የማያሻው በራሱ ውብ የሆነ ነው፡፡ ስነምግባሯም ትሁት እና ቅን ነው፡፡ የቆመችበት እግሯ ግን ሌጣውን ነው፡፡ 'ተረከዘ ሎሚ ጫማ የሌለሽ' በሚለው ስንኝ ውስጥ ግን እንደምንመለከተው ተረከዟ ምንም ውብ ቢሆን ጫማ የለውም፡፡ የጫማው አለመኖር ብቻ ሳይሆን በተናጋሪው ድምፀት ውስጥ ከቅሬታ የመነጨ አዘኔታም ይሰማል፡፡

በጥቅሉ ተናጋሪው በቀዳሚው ግጥም ፍከራ በትምህርት የተመሰለውን ከፍ ረዘም ያለ ጫማ አጥልቆላት ከምዕራባውያኑ ወይዛዝርት ጋር ያፎካከራት ያገሩን ልጅ ውብ ወጣት ነው፡፡ በስልጣኔ እና በትምህርቷ ብዙዎች እንዲንበረከኩላት ያደረጋት ተፈቃሪ ይህች ምስኪን ወጣት ነች፡፡

'ጫማ የሌለሽ' የሚለውም የዚህ ግጥም ሀረግ በቀዳሚው ግጥም ከራሷ በላይ ለዋለው ጥበባዊ ማንፈሻ እና ማበጠሪያ አክሊል መሰረት ይሆናት ዘንድ መሰረተ ድንጋይ እንዲጥልላት ያነሳሳው 'ያልሰለጠነችነቷ' እና 'ያልተማረችነቷ' መመሰያ ሆኖ ያገለገለ ይመስላል፡፡

## ጥበቃ - የፍቅር ማግስት

በግጥሞቹ ውስጥ የተገኘው የፍቅር ታሪክ አጋማሽ እድሜው ላይ የነበረበትን ሁነት የተረኩት 'እንዲያው ዝም' (23) እና 'ውኃ 'ማያጠፋው' (22) የሚሉት ግጥሞች ናቸው፡፡ ይህ ምዕራፍ ተናጋሪው የተፈቃሪዋን አዎንታዊ የፍቅር ምላሽ ሲማፀን እና በፍቅር ሲሰቃይ የሚታይበት ነው፡፡

## 3. እንዲያው ዝም

በዚህኛው ግጥም ውስጥ ተራኪው ለፍቅሩ መግለጫ የሚሆን አርኪ ነገር አጥቶ ዝምታን ዝምታን መርጦ እናገኘዋለን፡፡ የፍቅሩን ስሜት አይደረሴ ጥልቀትና ወሰን ድንበር አልባ ስፋት ሊያሳይ ሲጥር እናገኘዋለን፡፡ በግጥሙ ውስጥ የፍቅሩን ሃይል፣ ፅናት ጥልቀትና ስፋት ለመግለፅ የሚያስቸለውን መንገድ ሁሉ እያነሳ የሚጥል ተማራማሪ አፍቃሪ ሆኗል፡፡

’ወድሻለሁ ማለት አይጠቅም፤ አይበቃ፤
ፍቅሬ ነሽ ማለትም አይጠቅም፤ አይበቃ፤
ነፍሴ ነሽ ማለትም ልቤን አያርሰው፤
የፍቅራችን ነገር ዝም ነው፤ ዝም ነው፡፡
ምን ላርገው መውደዴን ለመግለፅ በሙሉ?
ልሳምሽ፤ ልቀፍሽ፤ ላልቅስ ወይ ላመሉ?
እግርሽን ልሳም ወይ፤ ልስገድልሽ ወይ?
ዓዋጅ ልናገረው በያደባባይ?
ወረቀት ልጻፍ ወይ፤ ልላክ ወይ ደብዳቤ
እያንዳንዱን ቃላት ወልጄ ከልቤ?
ገንዘቤን ልስጥሽ ወይ ሳይቆጨኝ መክሰሬ?
ልታረድ ልሰዋ፤ ለፍቅርሽ ለፍቅሬ?
ይህ ሁሉ ከንቱ ነው የልብ አያደርስም፡፡
በቃል ወይ በሥራ ፍቅር አይገለፅም፡፡
ይሻላል መሰለኝ እንዲያው ዝም እንዲያው ዝም፤
እንዲያው በደፈና፣ እንደ ሃይማኖት፤
ፍቅሬን ማወቅሽን ማመን መረዳት፡፡
(መንግስቱ ለማ፣ 23)

የግጥሙ አጠቃላይ ድምፀት ፍልስፍናዊ ጥያቄ ነው፡፡ የምርምር፣ የማጠየቅና ምላሽ የመሻት ጉጉት የሚነበብበት ነው፡፡ በዚህ ግጥም ውስጥ ተፈቃሪዋ ፊት ለፊት በገሃድ አልቀረበችም፤ የቀረበችው በአፍቃሪዋ ጥልቅ ስሜት ውስጥ ነው፡፡ ተራኪው ለሷ ያለውን ስሜት በቃላቱ ውዳሴና አድናቆት ሊገልጽላት ወይም አክብሮቱንና መስዋዕትነቱን ራሱን አዋርዶና ሰውቶ በተግባሩ ሊያሳያት የሚችልባቸው መንገዶች ሁሉ ሊያረኩት እንደማይችሉ የተገለፀላት፣ በቀዳሚዎቹ ግጥሞች ያየናት ተፈቃሪ ነች፡፡

ተራኪው በዚህ ግጥም ርዕስም ሆነ በግጥሙ ውስጥ ሊነግረን እየሞከረ ያለው ለተፈቃሪዋ ያለውን የፍቅር ስሜት አይገለፄ ባህሪና፣ ይህም የፍቅሯ ባህሪ ምንም ነገር ለማለት አለመቻልን፣ ሊባል የሚችል አንድም ነገር ማጣትን፣ እንዳስከተለበት ነው፡፡ የግጥሙ ማዕከላዊ ጉዳይ የቀረበው በግጥሙ 15ኛ ስንኝ ላይ ነው፡፡

በቃል ወይም በስራ ፍቅር አይገለፅም

ይህም ስንኝ ፍቅር እንዲህ በማለት ይገለፃል ወይም እንዲህ በማድረግ ይታወቃል ማለት እንደማይቻል የሚገልፅ ነው፡፡ ዝም ብሎ የሚታመን እንጂ በምርምር እንደማይደረስበት በአነፃፃሪ ዘይቤ በሃይማኖት መስሎ ያቀርበዋል፡፡

. . . . . .
እንዲያው በደፈና፣ እንደ ሃይማኖት፤
ፍቅሬን ማወቅሽን ማመን መረዳት፡፡

ሀይማኖት የሚለው ቃል በድፍኑ በአነፃፃሪ ዘይቤ ይቅረብ እንጂ፤ በምሰላው የቀረበው በስመ ሀዳሪ በሚባለው የዘይቤ አይነት ነው፡፡ መኖሪያውን ጠርቶ ነዋሪውን፣ ወይም ማደሪያውን ጠቅሶ አዳሪውን በሚገልጸው የዘይቤ ስልት የቀረበ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ዘይቤም ከተፃፈ ሀይማኖት ሲል ለመጠቀስ የፈለገው ሀይማኖት ውስጥ ያለውን ምስሶ

እግዚአብሔርን ሊሆን ይችላል፡፡ የፍቅርን ስሜት አይመረመሬነት፣ አይደረሴነትና ጥብቅ ምስጢራዊነት ከእግዝአብሔር ባህሪ ጋር በማወዳደር አቅርቦታል፡፡ በሀይማኖታዊ አስተምህሮዎች ‘‘የእግዝአብሔር ስራ አይመረመርም’’ እና ‘‘ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው’’ የሚለውን ምክር አዘል የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የሚያወሳ ይመስላል፡፡

ይህን ጥቅስ ለማውሳት ከሆነ፣ የእግዝአብሔርን ህልውና ወይም የመኖር ጥያቄ በየዋህነት የተባለውን ብቻ በመቀበል እንደሚታመነው ሁሉ የፍቅር ስሜትም የሚታወቀው በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ አርምሟዊ መረዳት በማካሄድ ነው፤ ስለዚህም ፍቅሬን ይህን አርምሞ በማካሄድ ተረጂኝ፣ የሚል ይመስላል፤ ተራኪው፡፡ የፍቅር ስሜት በሚባል ወይም በሚደረግ ነገር አይታወቅም፤ የሚለውን አመለካከት ተራኪው ያመነጨው በግል ተሞክሮው ላይ ካደረገው ጥልቅ ክትትል ይመስላል፡፡

ለተፈቃሪዋም ያስተላለፈው መልዕክት ፍቅሬን በምትሰሚውና በምታዩው፣ እንዲሁም በምነግርሽና በማደርግልሽ ነገሮች ላይ በምታደርጊው ምርምር ሳይሆን በደመነፍስሽ ተረጂኝ የሚል ነው፡፡

ተራኪው ለተፈቃሪዋ ያለው ክብርና ስሜት የተገለፀው በፍቅር ስሜቱ ውስጥ ነው፡፡ እንደ ፍቅር ስሜቱ ለሷ ያለው አጠቃላይ ስሜት ገደብና ወሰን የለውም፤ ፆታዊ ግንኙነቶችን ከሚወስኑ ባህላዊም ሆነ ግላዊ ወጎችና ተግዳሮቶችን የሚጥስ ነው፡፡ ባህላዊ ድንጋጌዎች ለየፆታው የደነገጉትን መሰረታዊ ገደቦች ደረማምሶ ሁሉ የልቡን ቢያደርስ የማይረካ መሆኑን ገልጿል፡፡ በግጥሙ ውስጥ ‘‘ላልቅስ ወይ ላመሉ?’’ ፣ ‘‘እግርሽን ልሳም ወይ፣ ልስገድልሽ ወይ?’’፣ ‘‘ገንዘቤን ልስጥሽ ወይ ሳይቆጨኝ መክሰሬ’’፣ ‘‘ልታረድ ልሰዋ’’ የሚሉት ሀረጎችና ስንኞች በባህሉ ባለቤቶች ዘንድ የሚያስወግዙትና የሚያሳፍሩት ድርጊቶች ቢሆኑ እንኳን ፣ ለተፈቃሪዋ ያንሳታል የሚል አቋም ተራኪው ይዟል፡፡

በዚህ ግጥም ውስጥ ተናጋሪው የሚለውን ነገር ያሳጣው ሀያል ፍቅር፣ በሚቀጥለው ግጥም ደግሞ ይህን የፍቅር ስሜት ይበልጥ እያናረበት ሲሄድ ይታያል፡፡

## 4. ውኃ ’ማያጠፋው

በቀዳሚዎቹ ግጥሞች ተራኪው በፍቅር ፍላፃ ሲወጋ፣ በፍቅር ፍላፃው የወጋውን የተፈቃሪዋን ድንግል፣ “ያልሰለጠነ” ውበት ተመለክተናል፡፡ በሦስተኛው ግጥም ውስጥ ደግሞ ፍቅሯ ተራኪውን “እንዲያው ዝም” እያለ ውስጥ ውስጡን ሲያብከነክነው ቆይቷል፡፡ በቀጣዩ ግጥም ደግሞ ውኃ የማያጠፋው እሳት ሆኖ ፍቅሯ ሲፈጀው፣ ሲያነደው፣ ሲያንበለብለውና ሲያቃጥለው የሚያሰማውን እሪታና ስቃይ እንሰማለን፡፡

**ውኃ ’ማያጠፋው** (መንግስቱ ለማ፣ 22)

ውኃ ’ማያጠፋው እሳት ነው ፍቅርሽ፡፡
ነደድኩኝ፡፡
ቢል አልኩኝ፡፡
ተቃጠልኩልሽ፡፡
ወደድኩሽ፡፡
ወደድኩህ በይኝ እባክሽ፡፡

የዚህን ግጥም ይዘትና መልዕክት ልናወጣ የምንችለው ቃላትንና ምሰላዎችን በመፈከር ብቻ አይደለም፤ ከቅርፅ አንፃርም ስንኞችን ስንተነትን ጭምር ነው፤ የተራኪውን መልዕክቶች በውል መገንዘብ የምንችለው፡፡ ምክንያቱም መልዕክቶች በግጥሙ ውስጥ የተላለፉት በስንኞች ቅርፅ እና አሰነኛኘት ጭምር ነው፡፡

በግጥሙ ከተላለፉት ፍቺዎች መካከል አንደኛው የሚገኘው በግጥሙ የመጀመሪያ ስንኝ እና በቀሪዎቹ ስንኞች መካከል የሚታየው እርዝምትና እጥረትም ራሱን የቻለ ፍቺ ያመነጫል፡፡ በግጥሙ ውስጥ እንደምናየው የመጀመሪያው ስንኝ ረጅም ነው፡፡ ይህም ርዝመት አንድም ተራኪው በፍቅሯ ሲማቅቅ እና ሲቃጠልበት የቆየበትን የጊዜ ርዝመት፤ አንድም በተራኪው ውስጥ ያለውን የፍቅሯን ይዞታ ስፋትና ርዝመት ሊገልፅ ይችላል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ስንኞቹ ከሚያወሱት የግጥሙ አካላት አንፃርም የስንኞቹን ርዝመት ተመልክተን ፍቺ ማፍለቅ እንችላለን፡፡ በቀዳሚው ረጅም ስንኝ ውስጥ የሚነገረን ውኃ በማያጠፋው እሳት በሆነ ፍቅሯ ተወክላ ስለቀረበችው ተፈቃሪ ነው፡፡ በሌሎቹ አጫጭር ስንኞች ውስጥ ሲቃጠል የምናየው ተራኪውን ነው፡፡ ይህም ርዝመትና እጥረት ተፈቃሪዋን አግዝፎ አፍቃሪውን ያኮሰመነ ይመስላል፡፡ ይህን የማግዘፍና የማኮስመን ቅርፃዊ ፍቺም እሷ ከላይ እርሱ ከስር በሆነበት የአቀማመጥ ትዕምርታዊ ፍቺ፣ የበላይነትና የበታችነትም ማጎላመስ እንችላለን፡፡

ውኃ ’ማያጠፋው እሳት ነው ፍቅርሽ፡

ነደድኩኝ፡፡
ቢል አልኩኝ፡፡
ተቃጠልኩልሽ፡፡
ወደድኩሽ፡፡

ወደድኩህ በይን እባክሽ፡፡

በዚህ ቅርፃዊ አቀማመጥ ውስጥ ተራኪው በግጥሙ የፍቅሩን ብርታትና ሃያልነት ብቻ አይደለም የገለፀው፤ ፍቅሯ ከጅምሩ የተደላደለ ስፋትና ርዝመት እንዳለውም በግጥሙ ቅርጻዊ ስንኞችም በጉልህ ተጨባጭ አድርጎ በግጥሙ የመጀመሪያ ስንኝ አቅርቦታል፡፡ ተፈቃሪዋን በገለፀበት በዚህ የመጀመሪያ ስንኝ ሁላ የመጡት ስንኞች የተናጋሪውን ሁነት የሚገልፁ ሲሆን አጫጭርም ናቸው፡፡ ይህም ቅርፅ ብቻውን የተፈቃሪዋን ግዝፈት ከተናጋሪው ጋር በማነጻጸር ይገልጻል፡፡

አሁንም ከቅርፃዊ ትንተና ሳንወጣ፣ ከስንኞቹ ዝግነትና ክፍትነት አንፃር ተጨማሪ ፍቺ እናገኛለን፡፡ ስለ ስንኝ ስናጠና ስንኞችን ከቅርፃቸው አንፃር ክፍት እና ዝግ ብለን እንከፍላቸዋለን፡፡ ሁሉም የግጥሙ ስንኞች የሚጨርሱት በአራት ነጥብ ነው፡፡ በስንኞቹ ውስጥ የቀረቡት ድርጊቶች ተደምድመው የሚያልቁት እዚያው ስንኝ ውስጥ ነው፡፡ ግጥሞች በዝግ ስንኞች የሚቀርቡት ያለምክንያት አይደለም፡፡ ሁሉም የተሟሉ ፍቺዎችን ሰጥተው በአንድ መስመር ውስጥ አልቀዋል፡፡ ስለዚህም ይህ ግጥም ሙሉ በሙሉ የቀረበው በዝግ ስንኞች ነው፤ ማለት እንችላለን፡፡

በግጥሙ ውስጥ የስንኞቹ ዝግ መሆን የግጥሙን ዋና ሀሳብና ፍቺዎች በውል ለመገንዘብ ያግዙናል፡፡ በእያንዳንዱ ስንኝ መጨረሻ ላይ የገቡት አራት ነጥቦች ግጥሙን ስናነብ ቆም ብለን ትንፋሽ እንድንወስድ ያስገድዱናል፡፡ በተለይም የተናጋሪው ሁነት የተነገረባቸው ስንኞች ተነባቢ ድምፆች (ቀለማት) እኩልና በአጭሩ ተነበው የሚያበቁ ናቸው፡፡ ተራኪው በአንዱ ስንኝ “ነደድኩኝ፡፡” ብሎ ሀሳቡን በአንድ ስንኝ ውስጥ ሲደመድም፣ እኛም ቆም ብለን፣ ትንፋሽ እንወስዳለን፡፡ ቀጥሎም “ቢል አልኩኝ፡፡”፣ ሲለን ቃጠሎውን እያሰብን ተግ እንላለን፡፡ ከዛም “ተቃጠልኩልሽ፡፡” የሚለውን ካነበብን

በኋላ አሁንም ቆም እንላለን፡፡ “ወደድኩሽ፡፡” እያለ ሲቀጥል የተራኪው ስቃይ ያፈነው እሪታ በየጊዜው እየበረታ ሲሄድ ለኛም ይሰማናል፡፡ በኃያል እሳት የተወከለው ፍቅሯም ሲያቃጥለው እኛም በተጨባጭ መመልከት እንድንችል ያደርገናል።

ግጥሙ የቀረበው እርዳታ በሚሻ የድረሽልኝ የተማፅኖ ድምፀት ነው፡፡ ውኃ ከማያጠፋው እሳት ሀያል ቅጣት ሊያድነው የሚችለው ብቸኛው ነገር የሷ “እወድሃለሁ” የሚለው ቃል ብቻ ነው፡፡ ተራኪው በፍቅሯ ፍላፃ ከተነደፈበት ቀን ጀምሮ እስካሁን “መውደድ” እንጂ “መወደድ” አልቻለም፤ “ወደድኩህ በይኝ እባክሽ፡፡” የሚለው የግጥሙ የመጨረሻ ስንኝም የሚገልፅልን ይህንን እውነታ ነው፡፡

ተፈቃሪዋ ውሃ እንኳን ሊያጠፋው በማይችል እሳት የተመሰለ ፍቅር ምንጭ ነች፡፡ ተራኪው የገባበት የፍቅር ረመጥ በሱ ላይ ብቻ ተወስኖ አይቀርም ወላፈኑ አንባቢን ይሰማዋል፡፡ በቃጠሎው ያሰማው እሪታ አንባቢውን ለእርዳታ ይጠራል፡፡ ተራኪው የፍቅር ስሜቱን አልጠላውም ፍቅሩ ረመጥ ሆኖ ቢፈጀውም ነበልባል ሆኖ ቢለበልበውም፤ ወዶታል፤ ፈቅዶታል፡፡ በቃጠሎው ውስጥ የሚሻው እሳት አደጋን ሳይሆን የተፈቃሪዋን አዎንታዊ ምላሽ ነው፡፡

### ስንብት - የፍቅር ፍፃሜ

ለረጅም ጊዜ የቆየው የፍቅር ታሪክ በተደጋጋሚ ጥልና ኩሪፊያ ውስጥ አልፎ በመሰናበት ሲቋጭ የሚያሳየው ምዕራፍ የተተረከው ‘ተጣልተን ተኳርፈን’ (56) እና ‘ጉድባይ’ (26) በሚሉ ርዕሶች በቀረቡት ግጥሞች ነው፡፡ በነዚህ ሁለት ግጥሞች የተናጋሪውን እና የተፈቃሪዋን የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ እንደ ፊልም ትዕይንት እንመለከታለን፡፡

## 5. “ተጣልተን ተኳርፈን”

በቀዳሚው ግጥም ተራኪው “ወደድኩህ በይኝ እባክሽ” በማለት ላቀረበው ተማፅኖ አልያም ለቀረበላት የፍቅር ጥያቄ ተፈቃሪዋ ለመጀመሪያ ጊዜ ምላሽ ስትሰጥ የምንሰማት በዚህ ግጥም ውስጥ ነው፡፡

ተጣልተን ተኳርፈን
ተኳርፈን ተቋርጠን
“ሴጣን ነህ” ብለሽኝ
“ሴት አይረባም” ብዬ
አንጎራጉራለሁ አፍዝዞኝ ስቃዩ:-
“አንቺ ልጅ አንቺ ልጅ አንቺ ልጅ አንችዬ!”

(መንግስቱ ለማ፣ “ተጣልተን ተኳርፈን”፣ 1955፡ 56)

በሌሎቹ ግጥሞች ውስጥ ተፈቃሪዋን የምናገኛት በተራኪው የፍቅር መንደፊያ ፍላፃዋ አማካይነት፣ ያገሩ ልጅ መሆኗን በገለፀበትና አካላዊ ውበቷ በተወደሰበት፣ ፍቅሯን መግለጥ አቅቶት በሚናውዝበት ዝምታ ውስጥ እንዲሁም እንደ ሲያል ረመጥ “ውኃ በማያጠፋው እሳት” ፍቅሯ ተራኪውን ስታንበለብለውና ስታነደው ነበር፡፡

በዚህኛው ግጥም ውስጥ ግን ተፈቃሪዋን ለመጀመሪያ ጊዜ በአንደበቷ ምላሽ ስትሰጥ እንሰማታለን፡፡ እስከዚህኛው ግጥም ድረስ ለተራኪው ፍቅር ምላሽ አልሰጠችም ነበር፡፡ አሁን ግን የተራኪው ፍቅረኛ መሆን እንደማትችል ገልፃለች፡፡

ይህ ግጥም ከርዕሱ ጀምሮ የሚያረዳን የተራኪውና የተፈቃሪዋን ፍቅር መጨረሻ ነው፡፡ በዚህ ግጥም ውስጥ ፍቅረኞቹ ከተጣሉና ከተኮራረፉ ብቻ ሳይሆን ከተቆራረጡም ብዙ ጊዜ ሆኗል፡፡ ተጣልተው ተኳርፈው ብዙ ጊዜ ሆኗቸዋል፡፡ በተደጋጋሚ ተጣልተው መኮራረፋቸውን፣ ተኮራርፈው መቆራረጣቸውን በሁለቱ የመጀመሪያ ስንኞች ተገልጾልናል፡፡

ተጣልተን ተኳርፈን
ተኳርፈን ተቋርጠን
...

ይህም ድርጊት ለረጅም ጊዜ ሲፈፀም እንደነበረ የምንረዳው ስንኞቹ ክፍት በመሆናቸው ነው፡፡ በእያንዳንዱ ስንኝ መጨረሻ ላይ ሥርዓተ ነጥብ አልገባም፤ ግጥሙ የተገነባው ከቀዳሚው ግጥም በተቃራኒው በክፍት ስንኞች ነው፡፡

በተራኪው ድምፀት ውስጥ ፀፀት ሲያንጎራጉር እንሰማዋለን፡፡ በግንኙነታቸው ላይ ተስፋ የቆረጠ ይመስላል፡፡ ነገር ግን መቁረጥ አቅቶታል፡፡ አሁን ላይ የሚነግረን የቆየውን ከረጅም ጊዜ በፊት በእሱና በተፈቃሪዋ መሀል የተፈጠረውን የመጨረሻ ጥል ነው፡፡ አሁንም ግን ከፍቅሯ ጋር በመንፈስ የተለየ አይመስልም፡፡

ከግጥሙ እንደምንረዳው ተራኪው ለረጅም ጊዜ ብቻውን ሲያፈቅራት ከቆየ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ (በቀዳሚው "ውኃ ማያጠፋው" ግጥም ውስጥ) ውደጅኝ ብሎ ሲጠይቃት፣ ልትወደው እንደማትችል ገልፃለታለች፡፡ ልትወደው ያልቻለችበትን ወይም የተጣሉበትን ምክንያት በግልፅና በቀጥታ አልተነገረንም፡፡ ነገር ግን ተጣልተው ተኮራርፈው ከቆዩ ከረጅም ጊዜ በኋላ፣ ተኮራርፈው ሲጣሉ፣ በሁለቱ ስንኞች ውስጥ፣ የተመላለሱት ቃላት ስለጥላቸው ምክንያት የሚገልጥ መልዕክት ያስተላለፉልን ይመስላል፡፡

..."ሴጣን ነህ" ብለሽኝ

"ሴት አይረባም" ብዬ...

## 6. "ጉድባይ"

ተራኪው ለመቁረጥ ተስኖት ለረጅም ጊዜ ከቆየ በኋላ መጨረሻ ላይ ለመቁረጥ የሚያስችለው በቂ ምክንያት ያገኘ ይመስላል፤ በዚህ ግጥም ውስጥ በገሀድ መሰናበት የቻለው፡፡ ይህ ግጥም ትንተና እና ፍከራ የሚያስፈልገው አይመስልም፡፡ የሁለቱ ፍቅረኛሞች የመጨረሻ እጣ ፈንታ ግጥሙ ራሱ ይነግረናል፡፡

**ጉድባይ**
ጉድባይ፤ ደህና ሁኚ፡፡
ጥፋቱስ አይደለም ያንቺ ወይም ከኔ
ፍቅር የመሆኑ ጽድቅና ኩነኔ፤
አንቺ አንችን መሆንሽ እኔ እኔን መሆኔ፤
ጉድባይ፤ ደህና ሁኚ፡፡
ሰላም ይሁን ይላል ልቤ ለልብሽ፤
ጉድባይ፤ ደህና ሁኚ፡፡
...
ፍቅርም እንደ ሰው፤ ወይም እንደ ከብት፤
እንዳትክልት፤ እንዳብቁልት፤ እንደ ወፍ፤ እንዳሣ
...
ፍቅርም እንደ ሰው
ተወልዶ፤ ነፍስ አውቆ፤ ጎርምሶ፤ ጎልምሶ፤
ግትቻ ይሆናል ደሞ ተመልሶ፡፡
...
ሴት ኳኳቴ ስትሆን ጭክ እንዳለች ዶሮ፤
አውራው ማምለጥ ሲመኝ ከሚላ ጋር በሮ፤
ያን ጊዜያት የሰው ልጅ
ማሳየት አለበት እንዳለው አእምሮ"

ጉድባይ ፤
ደህና ሁኚ ፡፡
(መንግስቱ ለማ፣ 1955፡ 26)

በዚህ ግጥም ውስጥ እንዳየነው ተፈቃሪዋና ተራኪው “ሴጣን ነህ”፣ “ሴት አይረባም” ተባብለው፤ ተኮራርፈው፣ ተለያይተው፣ ከተቆራረጡ ከረጅም ጊዜ በኋላ፣ ተራኪው መቀረጥ ችሏል፡፡ ተፈቃሪዋ ባለችበት ምድር ላይ ሆና ጭክ እንዳለች ዶሮ ስትንኳኳ፣ ተራኪው ግን በሰማይ ላይ ከሲላዎች ጋር በሮ ውኃ ከማያጠፋው ፍቅሯ መዳፍ ማምለጥ የቻለ ይመስላል፡፡

…
ሴት ኳኳቴ ስትሆን ጭክ እንዳለች ዶሮ፤
አውራው ማምለጥ ሲመኝ ከሢላ ጋር በሮ፤
ያን ጊዜያት የሰው ልጅ
ማሳየት አለበት እንዳለው አእምሮ”
ጉድባይ ፤
ደህና ሁኚ ፡፡

ይህንንም አቅም ሲያገኝ በተፈቃሪዋ ዘንድ ቅቡልነት ማግኘት ካልቻለው እሳታዊ ፍቅር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መፋታት ችሏል፡፡ በዚህም ማሰላሰል ውስጥ ለመቀረጥና ለመሳናበት ያስቻሉትን ምክንያቶች ዘርዝሮልናል፡፡

ከላይ ለማየት እንደሞከርነው ጥናቱ በዋናነት ንባብ ተኮር ትንተና አካሂዶ ግጥሞቹን ፈክሯል፡፡ ንባብ ተኮር ስነሂሳዊ ፍከራ፣ በተለይ የአንድን ሥነ-ጽሑፋዊ ሥራ አመጣጥ (አነሳስ) እና እድገት ለማጥናት አስፈላጊነቱ ጉልህ ነው (Guerin et.al, 2011)። በቀዳሚው ክፍል እንዳየነው በፍቅር ግጥሞቹ ላይ በተካሄደው ንባብ ተኮር የይዘት ፍከራ ወጥነት ያለው የፍቅር ታሪክ አነሳስ፣ እድገትና የመጨረሻ እጣፈንታ እንደገና ተዋቅሮ በትንተና ተተርኳል፡፡ ይህን አይነቱን ስነሂሳዊ መንገድ Ezra Pound የተባለ ሀያሲ፣ T. S. Eliot የተባለ ገጣሚ፣ The Waste Land በሚል ርዕስ፣ በተመሰቃቀለና በተበታተነ መንገድ ያቀረባቸውን ግጥሞች፣ ስነሂሳዊ አርትዖት የታከለበት ንባብ ተኮር ሂሳዊ ቀዶ ጥገና በማካሄድ፣ ወጥነት ባለው መንገድ ተለውጠው፣ ተስተካክለውና እንደገና ተዋቅረው እንዲቀርቡ በማድረግ፣ ስራው አድናቆትን ያተረፈ ምርጥ ዘመናዊ ስራ እንዲሆን አስችሎታል (Guerin et.al, 2011: 18-19)፡፡ ይህም ትንተና ግጥሞቹን በዚህ ስልት በመጠቀም በጊዜ ቅደም ተከተል እንደገና መተረክ በሚያስችል ሁኔታ ለማዋቀር ሞክሯል፡፡

የእያንዳንዱ ግጥም ተራኪ ነጠላ የፍቅር ግጥሞች አንዳቸው ከሌላው ጋር ሲናበቡ ስለአንድ የፍቅር ግንኙነት የሚተርኩ ወጥነት ያላቸው ትረካዎች መሆናቸውን፣ በግጥሞቹ ላይ የተደረገው ስነግጥማዊ ፍከራ አሳይቷል፡፡ ግጥሞቹ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና እየተለወጠ የሚሄድ ወጥ የፍቅር ታሪክን የሚተርኩ ቅደም ተከተላዊ ሂደት ተገኝቶባቸዋል፡፡ እያንዳንዱ ግጥም የአንድ ተናጋሪውን አንዲት ተፈቃሪ ሴት፣ የጊዜ ቅደም ተከተልን ጠብቆ የተቀረፀ ወጥ ምስል እና ተናጋሪው በተፈቃሪዋ ምክንያት የገባባቸውን ልቡናዊ ሁነቶች የሚያሳዩ፣ ግለ-ታሪኩንን የሚያነበንቡ ስነግጥማዊ ትዕይንቶች መሆናቸው ፍከራው አሳይቷል፡፡

ስድስቱም ግጥሞች በምዕራፍ ሊያደራጃቸው የሚያስችል፣ በጊዜ ቅደም ተከተል የተደራጀ የሚመስል፣ የአንድ ወጥ ታሪክ ተከታታይ ክፍሎችን አወቃቀር የሚያሳይ ንድፍ ተገኝቶባቸዋል፡፡ የሁሉም ግጥሞች ተፈቃሪ እንስት ምስል በሦስት ምዕራፍ ሊከፈል በሚችል ወጥነት ያለው ስነልቡናዊ ሁነቶች እና ተመሳሳይ ድባቦች ውስጥ ተቀርፃ በፍከራው ውስጥ ታይታለች፡፡ እነዚህ ሦስት ምዕራፎች ተፈቃሪዋ ልቡናዊ ቅርፅ እና ይዘት ተሰጥቷት ስትቀረፅ፣ በፍቅሯ ፍላፃ ተራኪውን ስትነድፈውና ስትፈቀር፤ ተራኪው በዝምታው ውስጥ በፍቅሯ ሲቆዝምና እንድትወደው ሲማፀናት፤

ተራኪውና ተፈቃሪዋ ሲጣሉ፣ ሲኮራረፉ፣ ሲቆራረጡና በስንብት ሲለያዩ ያሳያሉ፡፡ በነዚህም ምዕራፎች ውስጥ የሁለቱ ፍቅረኛሞች ፍቅር፣ ከፍቅራቸው ጅማሬ እስከ ፍቅራቸው ፍፃሜ ተተርኳል፡፡

# 4. ማጠቃለያ እና መፍትሔ ሀሳብ (Conclusion and recommendation)

ጥናቱ አንግቦት የተነሳው ዋነኛ ዓላማ የመንግስቱ ለማ የፍቅር ግጥሞችን መተንተንና መፈከር ነበር፡፡ በዚህም መሰረት "የግጥም ጉባኤ" በሚል ርዕስ በታተመው የግጥም መድብል ውስጥ የተቃራኒ ፆታን ፍቅር በርዕሰ ጉዳይነት ያነሱ 12 ግጥሞች መርጦ በ "ፈካሪ" (interpretative) የምርምር ስነዘዴያዊ ንድፍ በመከተል ስነሂሳዊ ትንተናና ፍከራ አድርጓል፡፡

በጥናቱ አንደኛ ዓላማ መሰረት በመድብሉ ውስጥ በተካተቱት የፍቅር ግጥሞች መሀል ተያያዥነት ያለው የፍቅር ታሪክ መተረኩን በምርመራው አረጋግጧል፡፡ በጥናቱ ሁለተኛ ንዑስ አላማ መሰረትም ወጥ ታሪክ የተገኘባቸው የፍቅር ግጥሞች እርስ በእርሳቸው እንዴት እንደሚገናኙ በፍከራ አሳይቷል፡፡ በግጥሞቹ ውስጥ የተተረከው የፍቅር ግንኙነትና ታሪክ በሦስት ምዕራፎች ውስጥ እንደሚያልፉ በማሳየትም የጥናቱን ሦስተኛ ዓላማ ከግብ አድርሷል፡፡

## 4.1. የጥናቱ ግኝቶች

ጥናቱ በመንግስቱ ለማ "የግጥም ጉባዔ" በሚለው የግጥም መድብል ውስጥ በተካተቱ የፍቅር ግጥሞች ላይ ባካሄደው ስነሂሳዊ ፍከራ

- በመድብሉ ውስጥ ከተካተቱት 26 ግጥሞች ውስጥ 12ቱ የፍቅር ግጥሞች መሆናቸው ተደርሶበታል፤
- በመድብሉ ውስጥ ከተካተቱት 12 የፍቅር ግጥሞች ውስጥ 6ቱ ወጥነት ያለው የፍቅር ታሪክ ሲተርኩ ተገኝተዋል፤
- "የፍቅር ፍላፃ" (25)፣ "ያገር ልጅ" (33)፣ "እንዲያው ዝም" (23)፣ "ውኃ ማያጠፋው" (22)፣ "ተጣልተን ተኳርፈን" (56) እና "ጉድባይ" (26) በሚሉ ርዕሶች የቀረቡት ግጥሞች የአንድ አፍቃሪና ተፈቃሪን የፍቅር ታሪክ እንደሚተርኩ ተደርሶበታል፤
- ተራኪው ለተፈቃሪዋ በሰጠው ምስልና ተፈቃሪዋ በገሀድ በተቀረፀችበት አሁናዊ ምስል መሀል ሰፊ ልዩነት እንዳለ መረጃዎች ጠቁመዋል፤
- የፍቅረኛሞቹ ፍቅር በፅንስነቱ የጨነገፈ ፍቅር እንደሆነ ተደርሶበታል፤
- በግጥሞቹ ውስጥ በቀጥታ ባይገለፅም ፍቅራቸው ለረጅም ጊዜ ከልጅነት እስከ ጉልምስና እድሜ የዘለቀ እንደነበር የሚያሳዩ ፍንጮች ተገኝተዋል፤

## 4.2. መፍትሔ ሀሳብ

የዚህ ጥናት አድማስ በሀገራችን የስነግጥም ታሪክ ውስጥ የተቃራኒ ፆታን ፍቅር እንደ ጭብጥ ይዞ በመነሳት "የመጀመሪያው" በሆነው መድብል ላይ ስነሂሳዊ ሂስ ፍከራ በማካሄድ ላይ የተወሰነ ነበር፡፡ በዋናነትም በዚህ መድብል ውስጥ በተካተቱት ግጥሞች ውስጥ ወጥነት ያለው የፍቅር ታሪክ እንደተተረከ አረጋግጧል፡፡ በግጥሞቹ ተራኪ እና ተፈቃሪ መሀል የነበረው ይህ ፍቅር የአንድ ጎልማሳ ሰው ግማሽ እድሜን ያህል ተጉዞ በመለያት እንደተደመደመ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት ብቻውን ሊሸፍናቸው የማይችላቸው ክፍተቶች እንዳሉ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ከእነዚህ ክፍተቶች መሀል የተወሰኑትን ለወደፊት አጥኚዎች ጥናቱ ይጠቁማል፡፡

ይህ ጥናት በግጥሞቹ ውስጥ የተተረከው የፍቅር ግንኙነት በመለያያት እንደተደመደመ እንጂ ለምንና እንዴት እንደተለያዩ አልገለጠም፡፡ ፍቅረኛሞቹን ለመለያየት ያበቃቸውን ምክንያት ሰፋ ያለ ትንተናና እና ፍከራ በማካሄድ ግጥሞቹን በመፈከር ማውጣት እንደሚቻል ለማስገንዘብ ይወዳል፡፡

በዚህ ጥናት ከተሰበሰቡ ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎች መካከል "በህፃንነታቸው ዝናሽ ትባል ከነበረችቷ ዘመዳቸው ጋር ሲጫወቱ ባደረባቸው አፍላጦናዊ ፍቅር ሳቢያ "ዘመናዊ የፍቅር ግጥሞችን" መጻፍ እንደጀመሩ ይታወቃል፡፡" (መስፍን ዓለማየሁ፣ 1988፡ 238) በሚል የተሰጠው አስተያየት አንዱ ነው፡፡ ይህንንም አስተያየት መሰረት አድርጎ የፍቅር ግጥሞቹን ከገጣሚው ህይወት ታሪክ ጋር አስተሳስሮ በስነልቡና ንድፈሀሳቦች የታገዘ ጥናት ቢደረግ ስለግጥሞቹም ሆነ ስለ ገጣሚው ብዙ ማወቅ እንደሚቻል ጥናቱ ያምናል፡፡

በአንድ ዘመን ስነፅሁፋዊ ስራዎች ውስጥ የሚንፀባረቁ ተመሳሳይ እና ተደጋጋሚ እውነታዎች ምንጭ የዘመኑ ማህበረሰብ ያፈራቸው ባህላዊና ማህበራዊ አቋሞች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከስነፅሁፋዊ ስራዎች ማህበረ-እውነታዊ ጭብጦችን ማርቀቅ እንደሚቻል የስነፅሁፍ ሃያሲያን ያስረዳሉ (Wellek & Warren, 1984: 102)። እነዚህን ግጥሞች መሰረት አድርጎ በዘመኑ የነበረውን አዲስ የስነፆታና የስነወሲብ አተያይ በወቅቱ ከነበረው ነባር የወል እሳቤ ጋር በማነፃፀር ማጥናት እንደሚቻልም ጥናቱ ይጠቁማል፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች (References)


መስፍን ዓለማየሁ፡፡ (አርታኢ)፡፡ *መንግስቱ ለማ - ደማሙ ብዕረኛ - (ግለ ታሪክ)*፡፡ አዲስ አበባ፤ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡ 1988፡፡

መንግስቱ ለማ፡፡ *የግጥም ጉባኤ ፡ የሐሳብ፣ የፍቅር፣ የተረት፣ የጨዋታ ግጥም*፡ አዲስ አበባ፡ ብርሃንና ሰላም፣ 1955፡፡

በዕውቀቱ ስዩም፡፡ *ስብስብ ግጥሞች*፡ አዲስ አበባ፡ አልፋ አታሚዎች፣ 1996፡፡

ብርሃኑ ገበየሁ፡፡ *የአማርኛ ስነግጥም*፡፡ አዲስ አበባ: አልፋ አታሚዎች፣ 1999፡፡

……… ፡፡ *''ዘመናዊው የአማርኛ ስነ-ግጥም፤ አንዳንድ ነጥቦች፡፡'' መድበለ ጉባኤ፡ የምዕተ አመቱ የኢትዮጵያ ስነፅሁፍ ዕድገት የንባብ ባህል ይዞታና የመጪው ክፍለ ዘመን ፈር*፡ አርትኦት ደረጀ ገብሬ፤ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ከግንቦት 27-28 1999 ባዘጋጀው ሴሚናር ላይ የቀረበ፡፡ አዲስ አበባ፡ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር፣ 2001፤ 166-203፡፡

የኢትዮጵያ መፅሐፍ ቅዱስ ማህበር፡፡ *መጽሐፍ ቅዱስ፤ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፡፡* አዲስ አበባ፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980፡፡

ደስታ ተክለወልድ፡፡ *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡* አዲስ አበባ፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962፡፡

Abrams, M.H. *Doing Things with Texts: Essays in criticism and critical theory*. Ed. Michael Filseler. W.W. Norton, E Company, 1991.

Carpenter, Laura M. "Analyzing Textual Material". *Handbook for conducting Research on Human Sexuality*. Eds. Michael W. Wiederman and Bernard E. Whitley. New Jersey: Lawrence Erlbaum Associates Publishers, 2002. 327-343.

Guerin, Wilfred; Earle Labor; Lee Morgan; Jeanne Reesman; John Willingham. *A Handbook of Critical Approaches to Literature*. 6th Edition. Oxford University Press Incorporated. 2011. ISBN-139780195394726

Mailloux, Steven. "*Interpretation*." In *Critical Terms for Literary Study*. Eds. Lentricchia, Frank and Thomas McLaughlin. 2nd ed. Chicago and London: The University of Chicago Press, 1995, 121-135.

Shmitz, Thomas A. *Modern Literary Theory and Texts.* Blackwell Publishing, 2007.

Wellek, Rene and Austin Warren. *Theory of Literature*. 3rd ed. New York: Harcourt Brace Jovanovich, Publishers, 1984.

Wiesner, Claudia. "Doing Qualitative and Interpretative Research: Reflecting Principles and Principled Challenges", Political Research Exchange, 2022, VOL. 4, 2127372; Published by Informa UK Limited, trading as Taylor & Francis Group. Published online: 28 Oct 2022. 4:1, 2127372, DOI:10.1080/2474736X.2022.2127372. https://doi.org/10.1080/2474736X.2022.2127372

Harla Journal of Social and Behavioral Studies gives access to this work open access and licensed under a Creative Commons Attribution-NonCommercial 4.0 International License.
(Creative Commons Attribution-NonCommercial 4.0 International License)